# የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ የአባላትና የአመራር አካላት አደረጃጀት፣ ተልዕኮና የአሰራር ጊዜያዊ መመሪያ

ግንቦት 2012

አዲስ አበባ

## መግቢያ

በብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ ላይ እንደተገለጸው ሊጉ ከእናት ፓርቲው የሚቀዳ የብልጽግና አደረጃጀት ነው፡፡ ህብረተሰባዊ ለውጥን የማፋጠን፤ የወቅቱን መድረክ ተልዕኮ ተገንዝቦ በብቃት የመፈፀም፤ ሁሉንም ሴቶች በጋራ አላማ የማሰለፍ፤ የትግል መድረክ ሆኖ የማገልገል፤ እና ጥቅሞችን የማጣጣም ቁልፍ እና ወሳኝ ተልዕኮ ይዞ የተቋቋመ የፖለቲካ አደረጃጀት ነው፡፡ ሊጉ ያነገባቸው አላማዎች የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካ ብልጽግና በመሆናቸው በተግባር ላይ ከዋሉ ሴቶች ከሚገኙበት ኃላቀርነትና ድህነት አላቆ ለፍትህ፣ ለእኩልነት፣ ለዲሞክራሲና ለብልፅግና ያበቃቸዋል፡፡

የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ሴቶች በሀገራችን በሚካሄደው ልማት ንቁ ተሣታፊና ከሚገኘው ኢኮኖሚ እድገት እኩል ተጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤ የሴቶችን ማሕበራዊ ተሣትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤ ሴቶችን ዝቅ አድርገው የሚመለከቱ አስተሣሰቦችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንዲሁም የሴቶችን የራሳቸውን የዝቅተኛነት አመለካከት ማስወገድ፤ የሴቶችን የሥራ ጫና ማቃለል እና ሴቶች በየደረጃው እኩል ፖለቲካዊ ተሣትፎና የውሣኔ ሰጪነት ሥልጣን እንዲኖራቸው በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና በህገ-መንግስቱ ዙሪያ ዘላቂ ተሣታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ላይ በማተኮር መታገልና ማታገል ይገባናል፡፡ በመሆኑም ሴቶች የራሳቸውን ተሳትፎና ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ሂደት ስትራቴጅክ ሀይል መሆናቸውን በመገንዘብ ግንባር ቀደም ሚና መጫወት እንዲችሉና የብልጽግና ፕሮግራማችና በተግባር ላይ ለመዋል እንዲቻል በሁሉም ደረጃ የሚሠራ አሠራርና አደረጃጀት መመሪያ ኖሮት በሙሉ አቅሙ መረባረብ ይኖርበታል፡፡

የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ተልዕኮው እና አሰራሩ ወጥነት እንዲኖረው እና አሁን ከደረስንበት የዕድገት ደረጃ በመነሳት በየደረጃ ያለውን የአመራር አካላት አደረጃጀት፤ ተልዕኮ እና አሰራር ለመወሰን የሚያስችል የተሟላ መመሪያ እስኪዘጋጅ ጊዜያዊ መመሪያ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፤ ከዚህ በፊት በተለያየ መዋቅር ተበታተነው የነበሩትን አደረጃጀቶች ሰብሰብ በማድረግና ሁሉንም በሚያካትት እንዲሁም የሊጋችንን ተልዕኮ እና የሀገራችን እኩልነት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የሊግ አደረጃጀት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል መነሻ መመሪያ በማስፈለጉ፤ መመሪያውን ከሊጉ ዋና ጽ/ቤት ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ ያለው አደረጃጀት እንዴት ተሳስሮ እና ተናቦ መሄድ እንዳለበት የሚያሳይና በጋራ በመደጋገፍ የሊጉን ተልዕኮና ሀገራዊ ለማሳካት በሚያግዝ መልኩ ማዘጋጀት በመታመኑ፤ በየደረጃው ያለው የሊጉ አመራር እና አባል በቀላሉ ለመጠቀም እንዲያስችለው በማሰብ የሊጉን መተዳደሪያ ደንብ በመከተል ይህ ጊዜያዊ መመሪያ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

## ክፍል አንድ

## የፌዴራልና የክልል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

### አንቀጽ 1፡- የፌዴራል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አመራር አደረጃጀት፣

የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ መተዳደሪ ደንብ እንደ ተጠበቀ ሆኖ የሊጉ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔዎችን ለማስፈፀም የፌደራል ሴቶች ሊግ አመራር አካላት አደረጃጀት የሚከተሉት ይሆናሉ፡ ፡

1. የሊጉ አስተባባሪ ኮሚቴ
2. የፌደራል ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ

### አንቀጽ 2፡ የሊጉ አስተባባሪ ኮሚቴ

የፌዴራል ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ፕሬዝዳንት ................................................ ሰብሳቢ
2. የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ምክትል ፕሬዝዳንቶች .........................................አባል
3. የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ኃላፊ ......................................................አባል
4. የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ የፖለቲካ ዘርፍ ሃላፊ ..........................................አባል
5. የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ....................................አባል፣

### አንቀጽ 3፡ የፌዴራል ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፣

1. በሊጉ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት የሊጉን የፖለቲካ እና የድርጅት ስራዎች በበላይነት ያስተባብራሉ፣
2. የሊጉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የማዕከላዊ ኮሚቴ ያወጣውን እቅድ አፈፃፀም ስራን ተከታትሎ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣
3. በፓርቲው እና በሴቶች ሊግ የሚካሄዱ ስልጠናዎችን ያቅዳል፣ ይመራል ይከታተላል፣
4. በየደረጃው ያሉትን የሊጉን አመራር አካላትን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልዕኳቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ የማብቃት ስራ ይሰራል፣
5. በሊጉ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የወጡ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ እንዲፈፀም ድጋፍ ይሰጣል፣
6. ስለ ስራው ክንውን ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ሪፖርት ያቀርባል፣
7. ጠንካራ የክትትና ድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት ስራን ይመራል፣

8. ተጠሪነቱ ለሊጉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 4. የፌደራል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ከዚህ ባጠረ ጊዜ ሊገናኝ ይችላል፡፡
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ በአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 5፡ የፌደራል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የፌደራል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ኃላፊ .................................................. ሰብሳቢ
2. የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ....................................ም/ሰብሳቢ
3. የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ .....................................አባል፣

## አንቀጽ 6፡ የፌደራል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፣

1. በሊጉ መተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ የፖለቲካ፣ የአደረጃትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. የሴቶች ሊግ አመታዊ መነሻ እቅድ በማዘጋጀት በማዕከላዊ ኮሚቴው ሲፀድቅ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፡፡ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል፡፡ ስለአፈፃፀሙም ለሴቶች ሊግ ፕሬዝዳንትና ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሪፖርት በማዘጋጀት ያቀርባል፣
3. በፓርቲዉ እና በሊጉ የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር የስልጠና ስራ ያጠናል፤ ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ስልጠናውንም እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡
4. የሊጉ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ችግሮችን ይለያል፣ መፍትሄ አቅጣጫ ይቀይሳል፡ ፡
5. የሴቶች ሊግ ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የስራ አፈፃፀም እና ዕቅድ በሚዲያና በህዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለህዝብ ያስተዋውቃሉ፡፡
6. የሊጉ አባላት ማህደር መረጃ፣ የሊጉን በጀት፣ንብረትና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራሉ፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፣
7. በስነምግባር የታነጸችና የመፈጸም አቅም ያላት ጠንካራ የሴት አመራርን በመፍጠር እና ለፓርቲዉ የሴት አመራር መፍለቅያ ለመሆን በበቂ ቁጥር ለማብቃት ያቅዳል፣ ይፈፅማል፡፡

8. የክልሉን ሴቶች ሊግ መዋቅርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣
9. የሊጉን የፋይናንስ ስራ ይከታተላል ይመራል ከዋና ፓርቲው ጽ/ቤት ጋር በቅንጅት የሊግ አባላቱን መዋጮ እና የተለያዩ ገቢዎችን ተከታትሎ ለአስተባባሪ ኮሚቴው ሪፖረት ያቀርባል
10. የክትትልና የድጋፍ ሥራ ያከናውናል፣
11. የሊጉ ልሳንና በራሪ ጽሁፎችን በመቅረጽ እና በፓርቲዉ ልሳን ውስጥ የሴት ሊግ አምድ እንዲካተት በማድረግ የአባላት ፖለቲካ ግንባታ አጀንዳዎችን በመቅረፅ ያስተላልፋል፡፡
12. የጽ/ቤቱን በጀት በማዘጋጀትና በፓርቲው ፋይናንስ ኮሚቴ በማቅረብ ሲጸድቅ በአግባቡ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
13. ተጠሪነቱ ለሴቶች ሊግ ፕሬዚዳንት ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 7፡ የፌደራል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባዔው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምፅ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካል ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡
4. ሳምንታዊ አጭር የስራ ግምገማ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ያደርጋል፡፡
5. በየሩብ አመቱ ከክልል ሴቶች ሊግ ጽ/ቤቶች ጋር መደበኛ ስብሰባ ያካሄዳል በየስድስት ወሩ ክልሎችን፣ ዞኖችንና ወረዳዎችን ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል በመውረድ ያያል፣ ይገመግማል ድጋፍ ይሰጣል፡፡

### አንቀጽ 8. የክልል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሠራር

የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ሴቶች ሊግ አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የክልል ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ
2. የክልል ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ

### አንቀጽ 9. የክልል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

የክልል አስተባባሪ ኮሚቴ 9 አባላት ያሉት በክልሉ ኮንፍራንስ የሚወከሉ/የሚመረጡ ሆነው ከመሀከላቸው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣሉ፡፡ የክልሉ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር አባላት በኮንፈረንሱ ባይመረጡም በአስተባባሪ ኮሚቴው መድረክ የሚሳተፉ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 10. የክልል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ከሴቶች ሊግ ብልጽግና ፓርቲ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የሴቶች ሊግ የፖለቲካ እና የድርጅት ሥራዎች በበላይነት ያስተባብራሉ፣
2. የሊጉ አስተባባሪ ኮሚቴ ዕቅድ አፈፃፀም ስራን ተከታትሎ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣
3. የብልፅግና ፓርቲንና የሊጉን እንዲሁም በመንግስት ስራዎችን ውስጥ የሴቷ ተጠቃሚነት እና ተሳታፊነት እንዲረጋገጥ ተግባራት ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣
4. በክልሉ የሚካሄዱ የፓርቲና የሊግ ስልጠናዎችን ሴቶች ያሳተፈ እዲሆን ያቅዳል፣ ይመራል ይከታተላል፣

5. የክልሉን ሴቶች የመፈጸም ብቃት በማዳበር በስነምግባር የታነጸችና የመፈጸም አቅም ያላት ጠንካራ የሴት አመራርን በመፍጠር እና ለፓርቲዉ የሴት አመራር መፍለቅያ ለመሆን በበቂ ቁጥር ለማብቃት ያቅዳል፣ ይፈፅማል፡፡

6. በሴቶች ሊግ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የወጡ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ እንዲፈፀም ድጋፍ ይሰጣል፣
7. የክልል የብልጽግና ሴቶች ሊግ አመራር እና በተዋረድ በሚሰጡ የሴቶች ሊግ ሹመት ለፓርቲ ጽ/ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ያሰማራል፣
8. የሊጉን የፋይናንስ ስራዎች ከፓርቲዉ የፋይናንስ አካላት ጋር በመቀናጀት የሊጉን የአባላት መዋጮ ይከታተላል፤ የደረሰበትን ይገመግማል፣
9. ስለ አጠቃላይ የሴት ሊጉ ሥራ ክንውን ለሊጉ ለኮንፈረንሱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
10. ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርአት በመዘርጋት ስራን ይመራል፣
11. ተጠሪነቱ ለሊጉ ስራ አስፈጻሚ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 11. የክልል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡ እንደአስፈላጊነቱ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊገናኝ ይችላል፡፡
2. ምልዓተ ጉባዔው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 12. የክልል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት

የክልል ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል

1. የክልል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ኃላፊ ……………………… ሰብሳቢ
2. የክልል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ……………… ም/ሰብሳቢ
3. የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ …………………..……… አባል

## አንቀጽ 13. የክልል ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. በሊጉ መተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የክልሉ ሴቶች ሊግ የፖለቲካዊ፣ የአደረጃጀትና የሕዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ከዋና ፓርቲ ጽ/ቤት የሚወርዱ ዕቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ክልል ሴቶች ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል፡፡
3. የአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የሴቶች ሊግ ሕዋስና መሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፡፡
4. በፓርቲው የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር ስልጠና የሴቶችን ተሳትፎ ምጥጥን በቂ  መሆኑን እና በአጠቃላይ የስልጠናውን ሁኔታ ይከታተላል፤ የሊጉን ስልጠናዎች ያቅዳል፣ ያደራጃል ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡
5. የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ችግሮችን ይለያል፣ የመፍትሔ አቅጣጫ ይቀይሳል፡፡
6. በሴቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የሊጉ ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የሥራ ዕቅዶች እና አፈፃፀም በሚዲያና በሕዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለሕዝብ ያስተዋውቃል፤
7. በክልሉ የሚገኙ የሴቶች ሊግ አባላት ማህደር መረጃ፣ የሊጉን በጀት፣ ንብረትና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራሉ፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፣
8. በስነምግባር የታነጸችና የመፈጸም አቅም ያላት ጠንካራ የሴት አመራርን በመፍጠር እና ለፓርቲዉ የሴት አመራር መፍለቅያ ለመሆን በበቂ ቁጥር ለማብቃት ያቅዳል፣ ይፈፅማል፡፡
9. የዞን የከተማና የወረዳ የሴቶች ሊግ አመራርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፡፡
10. የሊጉን የፋይናንስ ስራዎች ከፓርቲው የፋይናንስ ዘርፍ ጋር በመቀናጀት ይከታተላል ደግፋል የአባላቱን መዋጮ እና አጠቃላይ የሊጉን ገቢ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

11. የክትትልና ድጋፍ ሥራ ያከናውናል፡፡
12. ለብልጽግና ሴቶች ሊግ ልሳንና በራሪ ጽሑፎች ለሚካሄደው የአባላት ግንባታ አጀንዳዎችን በመቅረጽ ያስተላልፋል፡፡
13. የጽ/ቤቱን በጀት በአግባቡ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣
14. ተጠሪነቱ ለክልሉ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴና ለፌደራል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 14፡ የክልል ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር፣

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡
4. ሳምንታዊ አጭር የስራ ግምገማ፣ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ይደረጋል፡፡
5. በየወሩ በክልሉ ካሉት ዞኖችና ለክልል ተጠሪ የሆኑ ከተሞችን በየ6 ወሩ ወረዳዎችን ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል በመውረድ ያያል፣ ይገመግማል ድጋፍ ይሰጣል፡ ፡
6. ለብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት በ2 ሳምንት የስራ ኢንፎርሜሽን ልውውጥ ያደርጋል፣ በወር አጭር የፅሑፍ ሪፖርት፣ በየ3 ወሩ አጠቃላይ የስራ ሪፖርትና የጋራ መድረክ ይኖረዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የዞን/የልዩ ወረዳ ሴቶች ሊግ አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

### አንቀጽ 15፡ የዞን/የልዩ ወረዳ ሴቶች ሊግ አመራር አካላት አደረጃጀት

የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ የዞን/የልዩ ወረዳ ሴቶች ሊግ አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የዞን/የልዩ ወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ
2. የዞን/የልዩ ወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ

## አንቀጽ 16. የዞን/የልዩ ወረዳ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

የዞን/የልዩ ወረዳ አስተባባሪ ኮሚቴ የዞን/የልዩ ወረዳ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ኮንፍራንስ የሚመረጡ 7 አባላት ያሉት ሆኖ ከመሀከላቸው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣሉ። የዞን/የልዩ ወረዳ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት የአመራር አባላት በኮንፈረንሱ ባይመረጡም በአስተባባሪ መድረኩ የሚሳተፉ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 17. የዞን/የልዩ ወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ከክልሉ ሴቶች ሊግ አሰተተባባሪ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የሴቶች ሊግ የፖለቲካ እና የድርጅት ሥራዎችን የእለት ተእለት እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል
2. የሊጉን ዕቅድ አፈፃፀም ስራን ተከታትሎ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣
3. የብልፅግና ፓርቲንና የሊጉን እንዲሁም በመንግስት ስራዎችን ውስጥ የሴቷ ተጠቃሚነት እና ተሳታፊነት እንዲረጋገጥ ተግባራት ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣
4. የዞን/የልዩ ወረዳ የሚካሄዱ የፓርቲና የሊግ ስልጠናዎች ሴቶችን ያሳተፈ እዲሆን ያቅዳል፣ ይመራል ይከታተላል፣
5. የሴት አመራር የመፈፀም ብቃትን በማዳበር የሴት አባላትን የተደራጀ እንቅስቃሴ የምትመራ ጠንካራ የሴት አመራርን በመፍጠር እና ለፓርቲዉ የሴት አመራር መፍለቅያ በመሆን በበቂ ቁጥር ለማብቃት ያቅዳል፣ ይፈፅማል፡
6. በክልሉ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ የወጡ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ እንዲፈፀም ድጋፍ ይሰጣል፣
7. የዞን/የልዩ ወረዳ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አመራር እና በተዋረድ በሚሰጡ የሴቶች ሊግ ሹመት ለፓርቲ ጽ/ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ያሰማራል፣
8. የዞኑን/የከተማዉን የሊግ አባላቱን ገቢዎች ይከታተላል ሪፖርቱን ይገመግማል አቅጣጫ ይሰጣል፡
   :
9. ስለ ሥራው ክንውን ለሊግ ለኮንፈረንስ እና ለክልሉ ብልጽግና ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል።
10. ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርአት በመዘርጋት ስራን ይመራል፣
11. ተጠሪነቱ ለዞኑ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ኮንፈረንስና ለክልሉ ሊግ አስተባባሪ ይሆናል።

## አንቀጽ 18. የዞን/የልዩ ወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. ቢያንስ በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል።
2. ምልዓተ ጉባዔው 50+1 ነው።

3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 19. የዞን/የልዩ ወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት

የዞን/የልዩ ወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል

1. የዞን/የልዩ ወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ኃላፊ …………… ሰብሳቢ
2. የዞን/የልዩ ወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ……… ም/ሰብሳቢ
3. የ የዞን/የልዩ ወረዳ ብ/ፓርቲ ሴቶች ሊግ አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ……… አባል

## አንቀጽ 20. የዞን/የልዩ ወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. በሊጉ መተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የዞን/የልዩ ወረዳ ሴቶች ሊግ የፖለቲካዊ፣ የአደረጃጀትና የሕዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ከክልል ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት የሚወርዱ ዕቅዶችን መነሻ በማድረግ የዞን/የልዩ ወረዳ ሴቶች ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል፡፡
3. የአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የሴቶች ሊግ ሕዋስና መሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፡፡
4. በፓርቲው በሚካሄደውን የአባላትና የአመራር ስልጠና የሴቶችን ተሳትፎ ምጥጥን መሆኑን እና በአጠቃላይ የስልጠናውን ሁኔታ ይከታተላል፤ የሊጉን ስልጠና ያቅዳል፣ ያደራጃል በስልጠናው ሴቶች እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡
5. የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል፤ ችግሮችን ይለያል፤ የመፍትሔ አቅጣጫ ይቀይሳል፡፡
6. በሴቶች ሊግ እና በፓርቲውጽ/ቤት በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የሊጉ ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የሥራ አፈፃፀም እና ዕቅዶች በሚዲያና በሕዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለሕዝብ ያስተዋውቃሉ፣
7. የዞን/የልዩ ወረዳ የሚገኙ የሴቶች ሊግ አባላት ማህደር መረጃ፣ የሊጉን በጀት፣ ንብረትና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራሉ፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፣

8. በስነምግባር የታነጸችና የመፈጸም አቅም ያላት ጠንካራ የሴት አመራርን በመፍጠር እና ለፓርቲዉ የሴት አመራር መፍለቅያ ለመሆን በበቂ ቁጥር ለማብቃት ያቅዳል፣ ይፈፅማል፡፡

9. የከተማና የወረዳ የሴቶች ሊግ አመራርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፡፡
10. የሊጉን ገቢዎች ይከታተላል፡ ያስፈጽማል ከዞኑ ብልጽግና ፓርቲ ጸ/ቤት ጋር በቅንጅት ገምግሞ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
11. የሚከተለውን የክትትልና ድጋፍ ሥራ ያከናውናል፡-

- በ2 ሳምንት የስራ ኢንፎርሜሽን ልውውጥ ያደርጋል፣ በወር አጭር የፅሑፍ ሪፖርት፣ በየ3 ወሩ አጠቃላይ የስራ ሪፖርትና የጋራ መድረክ ይኖረዋል፡፡ ለዚህም የግምገማ እና ሂስ እና ግለ ሂሲ ተደርጎ ኦርኔል ይሞላል፡፡

12. በብልጽግና ሴቶች ሊግ ልሳንና በራሪ ጽሑፎች የሚተላለፉትን መልህክቶች ከዞኑ እና ከከተማ አሰተዳደሩ ጋር አጣትሞ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
13. ተጠሪነቱ ለክልሉ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ለክልሉ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 21. የዞን/የልዩ ወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር፣

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ የሚጸድቅ ይሆናል፡ ፡
4. የወረዳ/የከተማ/ቀበሌ ሴቶች ሊግ አመራርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፡፡

ሀ) በየሩብ አመቱ ከወዳ/ከተማ/ቀበሌ ጽ/ቤት ሴቶች ሊግ አመራር ጋር የስራ ግምገማ ያደርጋል፡፡

ለ) በየወሩ ወረዳዎች/ቀበሌዎች ያሉበት የአፈፃፀም ደረጃ የጽሁፍ ሪፖርት ተቀብሎ ተገቢውን ግብረ መልስና ድጋፍ ይሰጣል፡፡

ሐ) በየሳምንቱ ከወረዳዎች/ቀበሌዎች ጋር በስልክ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ኢንፎርሜሽን ይቀበላል፡፡

መ) አመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማና የቀጣይ አመት እቅድ ለወረዳ/ከተማ/ቀበሌ ለሊግ አመራር ኦረንቴሽን ይሰጣል፡፡ በየ3 ወሩ ደግሞ ከጠንካራ፣ መካከለኛና ደካማ ወረዳዎች/ቀበሌዎች

ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል ይገመግል የድጋፍ አቅጣጫንም ያስቀምጣል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

### አንቀጽ 22. የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አመራር አካላት አደረጃጀት፣

የወረዳ ሴቶች ሊግ አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ፣
2. የሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ

### አንቀፅ 23. የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ በወረዳው ኮንፍራንስ የሚመረጡ 7 አባላትን የሚኖሩት ሆኖ ከመሀከላቸው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣሉ፡፡ የወረዳው ሴት ሊግ ጽ/ቤት አመራሮች በኮንፍራንሱ ባይመረጡም በአስተባባሪ ኮሚቴው መድረክ የሚሳተፉ ይሆናሉ፡፡

### አንቀጽ 24. የወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ከዞን ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የወረዳውን የሴቶች ሊግ የፖለቲካ ስራና የመንግስት ስራዎችን የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ይከታተላል፤ ይመራል፣
2. በወረዳው የሚካሄዱ የሴቶች ሊግ፣ የፓርቲና የመንግስት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይከታተላል፣ በህዴቱም የሴቶች ተሳትፎ መሟላቱን ያረጋግጣል፤ የቀበሌ የሴት ሊግ አመራር አካላትን በቅርብ ይደግፋል፡፡
3. የሴቶች ሊግ አባላት እና የሴት አመራር አካላትን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልዕኳቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ ጠንካራ ስራ ይሰራል፡፡
4. የሴቶች ሊግ አመራር ምደባ የውሳኔ ሀሳብ በወረዳዉ ላለው የፓርቲ ጽ/ቤት ያቀርባሉ፣ ሲጸድቅ ያስማራሉ፣
5. ከሊጉ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የወጡ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ያስፈፅማል፣ ይፈፅማል፡፡
6. ተጠሪነቱ ለዞን አስተባባሪ ኮሚቴ እና ለዞኑ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 25. የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡ በሚቀጥሉት 15 ቀናት ውስጥ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 26. የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የወረዳ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ኃላፊ ........................................... ሰብሳቢ
2. የወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ............................ም/ሰብሳቢ
3. የወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ................................ አባል

## አንቀጽ 27. የወረዳው ብልጽግና ፓርቲ የሊጉ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የሊጉ ጽ/ቤት በመተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የወረዳ የፖለቲካ፣ የአደረጃጀትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ከዞን ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት የሚወርዱ እቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚውን አካል ኦረንቴሽን ሰጥቶ ያሰማራል፣ የስራውን አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይመራል፣
3. የሊግ አደረጃጀት አመራርና አባላት በስራቸው ግምባር ቀደም እንዲሆኑ ፖለቲካዊ ግንዛቤያቸው እንዲዳብር ያደርጋል፣
4. በወረዳው የሊግ አባላት የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራዎች ከመተግበር አኳያ ያሉ መልካም ልምዶችን ይቀምራል እንዲስፋፉ ያደርጋል፡
5. የአባላት የእለት ተእለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የሴቶች ሊግ አባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የሊግ የህዋስና መሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይመራል፣
6. በወረዳ የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር ስልጠና፣ ሴሚናር፣ የመ/ድርጅቶች ኮንፈረንስ ያስተባብራል፣ ይመራል፣

7. የሊጉ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ያስፈፅማል፣ ይፈጽማል፣
8. በወረዳ ውስጥ በሚገኙ ሊጉ የአባላት ማህደር መረጃ የሊጉ ሰነዶች ገንዘብና ንብረት በበላይነት ያስተዳድራል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
9. በስነምግባር የታነጸችና የመፈጸም አቅም ያላት ጠንካራ የሴት አመራርን በመፍጠር እና ለፓርቲዉ የሴት አመራር መፍለቅያ ለመሆን በበቂ ቁጥር ለማብቃት ያቅዳል፣ ይፈፅማል፡፡
10. በልሳናትና በራሪ ጽሁፎች እንዲሁም በብልጽግና መጽሄት ላይ ለሚካሄደው የአባላት ግንባታ ከዞን ፓርቲ ጽ/ቤት የሚተላለፉትን ከወረዳ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ያደርጋል፣
11. የሊጉን የገቢ ሰርዓት መራል ይከታተላል ሥላ አባላቱ መዋጮ ከፓርቲዉ ፋይናንስ ክፍል ጋር በቅንጅት ሪፖርት አቅርቦ ይገመግማል
12. ተጠሪነቱ ለዞን አስተባባሪ ኮሚቴና ለዞን/ለከተማ አስተዳደር ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 28. የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## የአዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ለክልል ተጠሪ የሆኑ ከተሞች የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

### አንቀጽ 29፡ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አመራር አካላት

የከተማ/አስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ አመራር አካላት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የከተማ የአስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ፣
2. የከተማ የአስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ

## አንቀጽ 30፡ የከተማ የአስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

የከተማ/የአስተዳደሩ የሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ በከተማ አስተዳደሩ ሴቶች ሊግ ኮንፍረንስ የሚወከሉ/የሚመረጡ 9 አባላት ያሉት ሆኖ ከመሀከላቸው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣሉ፡፡ የከተማዉ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር አባላት በኮንፍራንሱ ባይመረጡም የአስተባባሪ ኮሚቴው መድረክ ተሳታፊዎች ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 31. የከተማ አስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ከፌደራል ሴቶች ሊግ አስተባባርና ከሊጉ ጽ/ቤት በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የከተማውን የሴቶች የፖለቲካ ስራና የመንግስት ስራዎች በሴቶች ዙሪያ ያለዉን የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ይከታተላል ይመራል፣
2. የከተማ/አስተዳደሩ የፓርቲ ጽ/ቤት እንዲሁም የሊጉ አሰተባባሪ ኮሚቴ አጠቃላይ የአመራር ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በተሟላ መንገድ በስራ ላይ እንዲውሉ መከታተል፣ ማስፈፀም፣ መፈፀም
3. በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ የሴት አደረጃጀቶች እና መሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ አመራር በስሩ ያሉትን አባላት አደራጅቶ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል አቅም እንዲኖረው ማስቻል፣ የአደረጃጀቶችን ጥሩ ልምድ እና ተሞክሮ ቀምሮ እንዲሰፋ ያደርጋል፡፡
4. የከተማ የአስተዳደሩን የብጽና ፓርቲ ሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ አመራር አካላት በሊጉ አደረጃጀትና የአሰራር መመሪያዎች ላይ በቂ ግንዛቤ ይዞ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
5. በከተማው አስተዳደሩ በሚካሄዱ ኢንቨስትመንት፣ ለመካከለኛና አነስተኛ የማምረትና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት መስፋፋት ምቹ ሁኔታ ከሚፈጥሩ አካላት ጋር የሴቶች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤ የስራ እድልን ማስፋት፣ የሴቶች መልካም አስተዳደር ችግርን መለየት፣ የከተማው የመኖሪያ ቤት እጥረት እንዲቀረፍ ሲሰራ እና በከተማው የቤት መስሪያ ቦታም ሆነ መስሪያና መሸጫ መሬት ወይ ሼድ ሲሰጥ ሴቶችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ መፈጸሙን መከታተልና ተፈጻሚ እንዲሆን መስራት፡፡
6. የአዲስ አበባና የድሬዳዋ የሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነታቸው ለፌደራል ሴቶች ሊግ ስራ አስፈፃሚና ለሴቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት ሲሆን የተቀሩት ከተሞች ሊግ አስተባባሪዎች ተጠሪ ለሆኑለት መዋቅር አስተባባሪ ኮሚቴ እና ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 32. የከተማ የአስተዳደሩ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር፣

1. አስተባባሪ ኮሚቴው በየ15 ቀኑ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡ በመደበኛ ስብሰባው የሚከተሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይወያያል፡፡

ሀ) በ15 ቀን ውስጥ በከተማው አስተዳደሩ በሴቶች ሊግ የተከናወኑ ስራዎችን የነበሩትን ጠንካራ እና ደካማ እንቅስቃሴዎች ግምገማ ያደርጋል፡፡

ለ) ከግምገማው በመነሳት በቀጣይ 2 ሳምንት ትኩረት የሚሰጣቸው አቅጣጫዎች ይቀይሳል፡

2. የወር፣ የሩብ አመትና አመታዊ ግምገማዎችን ያካሂዳል ግብረ መልስ ይሰጣል የቀጣይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡
3. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
4. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 33. የከተማ የአስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ

የከተማው አስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የብልጽና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ኃላፊ ....................................................... ሰብሳቢ
2. የብልጽና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ...........................................ምክትል
3. የብልጽና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ -------------------- አባል

## አንቀጽ 34. የከተማው አስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የሊጉ ጽ/ቤት በመተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የከተማው ሴቶች የፖለቲካ፣ የአደረጃጀትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ከፌዴራል ሴቶች ሊግ እና ከአስተባባሪ ኮሚቴዉ የሚወርዱ እቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ከተማ ሴቶች ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚውን አካል ኦረንቴሽን ሰጥቶ ያሰማራል፣ የስራውን አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይመራል፣
3. መሰረታዊ ድርጅቶችና ህዋሳት በአደረጃጀታቸው ጠንካራና ተልዕኮ ፈፃሚ ሆነው እንዲወጡ የሚያስችል ድጋፍና አመራር መስጠትና ፖለቲካዊ ግንዛቤያቸውን እንዲዳብር ይሰራል፡፡
4. በከተማ አስተዳደሩ የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራዎች ከሴቶች አኳያ ያሉ መልካም ልምዶችን እና ድክመቶችን በመለየት መልካሙ እንዲስፋፉ ድክመቶቹ እንዲሻሻሉ ያደርጋል፡፡
5. የሊጉ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በከተማው አስተዳደሩ በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ያስፈፅማል፣ ይገመግማል፣ ይፈጽማል፣

6. በከተማው/በአስተዳደሩ ውስጥ በሚገኙ የሴት አባላት ማህደር፣ መረጃ የሊጉ ሰነዶች የሊጉ ንብረት እና በጀት በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
7. የብልጽግና ፓርቲ በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው ተቀባይነት ጨምሮ የሊጉ አባላት ህብረተሰቡ ግንባር ቀደምእንዲሆኑ፣ፖለቲካዊ ብቃታቸው እንዲዳብር እና በአቋማቸዉ ጠንካራ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
8. ሌሎች የሴቶች አደረጃጀትን በማጠናከር ዴሞክራሲያዊ የሴቶች አደረጃጀት እንዲሆኑና ጠንካራ የሴት አመራሮች መፍለቂያ እንዲሆኑ ይሠራል፡፡
9. የሊጉ መሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ አመራር አቅም ግንባታ ስራዎች ያሉበትን ደረጃና ችግሮች ይገመግማል፣ የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡
10. የሊጉን የፋይናንስ ስርዓት ይከታተላል የተለያዩ የሊጉን ገቢዎች ከፓርቲው ፋይናንስ ሰራተኞች ጋር በቅንጅት አፈጻሙን ተከታትሎ ሪፖርት ያቀርባል
11. አዲስ አበባ እና ድሬደዋ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ተጠሪነታቸው ለከተማ ለአስተዳደሩ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴና ለብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት ይሆናል፡፡ ሌሎች ከተሞች ሊግ ጽ ቤቶች ተጠሪነታቸው ተጠሪ ለሆኑበት ክልል የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪና ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 35. የከተማ አስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. የሊጉ ጽ/ቤት ሳምንታዊ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ የሚጸድቅ ይሆናል፡ ፡
4. በሳምንቱ በከተማው/በአስተዳደሩ የሴቶች ሊግ ፖለቲካዊና የአደረጃጀት ስራዎች የነበሩትን ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች አስመልክቶ ግምገማ ያደርጋል፡፡ አቅጣጫም ያስቀምጣል፡፡
5. አስተባባሪ ኮሚቴው በየ15 ቀኑ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣

## አንቀጽ 36. የአዲስ አበባ ክፍለ ከተማ የሴቶች ሊግ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የክፍለ ከተማ የሴቶች ሊግ ብልጽግና ፓርቲ አመራር ኮሚቴ በክፍለ ከተማው የሊጉ አባላት ኮንፍራንስ የሚወከሉ 7 አባላት ያሉት ሆኖ ከመሀከላቸው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣሉ፡፡ ከሊጉ ጽ/ቤት አመራር አባላት በኮንፍራንስ ባይመረጡም የአስተባባሪ ኮሚቴው መድረክ ተሳታፊዎች ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 37. የክፍለ ከተማ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፣

1. ከከተማ የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የክፍለ ከተማውን የሊጉን የአደረጃጀትና የፖለቲካ ስራዎች እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይመራል፡፡
2. የከተማ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ያወጣውን እቅድ አፈፃፀም ስራን ተከታትሎ ያስፈፅማል፣ ይፈፅማል፡፡
3. ሊጉ በፓርቲና በመንግስት ስራዎች የሴቷ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነት መረጋገጡን ይከታተላል፤ ስራዎቹ ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፡፡
4. በየወረዳ እና በየክፍለ ከተማ በሴቶች አደረጃጀት እና በሊጉ የተገኙ መልካም ልምዶችን በመቀመር እንዲሰፋ ያደርጋል፣
5. በክፍለ ከተማ የሚካሄዱ የሊጉ፣ ፓርቲና የመንግስት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይከታተላል፣ የሴቶችን ተሳትፎ ያረጋግጣል፣ ይመራል፣
6. በክፍለ ከተማ ያሉትን የሴት ሊግ አባላተት፣ አመራሮች እና አጠቃላይ የሴት የመንግስት አመራሮችን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልእኳቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ የማብቃት ስራ ይሰራል፡፡
7. የወረዳ የሴት ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴና የሊግ አመራር አባላት ምደባ የውሳኔ ሃሳብ ቀጥሎ ላለው የፓርቲ ጽ/ቤት ያቀርባሉ፣ ሲፀድቅ ያስማራሉ፣
8. ስለ ስራው ክንውን ቀጥሎ ላለው የሴት ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣ የመልካም ልምዶችን የማስፋት ስራው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይገመግማል፡፡ ለችግሮችም የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡
9. የመንግስትና ፓርቲ ስራዎች የሴቶችን ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት በተገቢው መንገድ ተቀናጅተው ለማረጋገጥ እየተሰሩ መሆናቸውን ይገመግማል፡፡
10. የሊጉ የአሰራርና አደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይገመግማል፡፡
11. ተጠሪነቱ ለከተማው ሴት ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ለከተማዉ ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 38. የክፍለ ከተማ የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 39. የክፍለ ከተማ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የክፍለ ከተማ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የሊጉ ጽ/ቤት ኃላፊ ........................................................................................ ሰብሳቢ
2. የሊጉ ፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ....................................................................ም/ሰብሳቢ
3. የሊጉ አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ .........................................................................አባል

## አንቀጽ 40. የክፍለ ከተማ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የክፍለ ከተማዉ ሴቶች የፖለቲካ፣ የአደረጃጀትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣
2. ከከተማ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት የሚወርዱ እቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ክፍለ ከተማ ሴቶች ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የሴቶችን ፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል፡፡
3. በክፍለ ከተማ የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የአደረጃጀትና የፖለቲካዊና ፓርቲ ስራዎች ውስጥ በሴቷ በኩል የሚታዩ መልካም ልምዶችን በመለየት በመቀመር እንዲስፋፉ ያደርጋል፡ :
4. የሊጉን አባላት የእለት ተእለት ግንባታ ስራን እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የሊጉ ህዋስና መሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል፣ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፣
5. በሊጉ እና በፓርቲው የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር የስልጠና የሴቷ ተሳትፎ ምጥጥን እንዲረጋገጥ ያደርጋል፣ ያደራጃል ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡
6. በከተማው የሊግ ጽ/ቤት በሚሰጡ አቅጣጫዎች መሰረት የሊጉን ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የስራ እቅዶች እና አፈፃፀም በሚዲያና በህዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለህዝብ ያስተዋውቃሉ፣
7. በሊጉ ልሳንና በሚወርዱ ጽሁፎች ላይ ተመስርቶ ለሚካሄደው የአባላት አቅም ግንባታ አባሎቻችን በተገቢው መሳተፋቸውንና ተደራሽነቱን ይከታተላል ስራውን ያስፈፅማል፣
8. የሊጉን የገቢ እና የፋናንስ ስራ በበላይነት ይመራል ከፓርቲው የፋይናንስ ሰራተኞች ግር ያለበትን ይከታተላል ሪፖርት ያቀርባል፡፡
9. የታቀዱ ስራዎች አፈጻጸም ይገመግማል፣ ድጋፍ ይሰጣል፡፡
10. ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ለከተማ ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 41. የክፍለ ከተማ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡
4. የወረዳ የሴት ሊጉን አመራር በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፣

   ሀ) በየሩብ አመቱ ከወረዳ ሴቶች ሊግ አመራር ኮሚቴ ጋር የስራ ግምገማ ያደርጋል፡

   ለ) በየወሩ ከወረዳ የሴት ሊግ አመራር ጋር የአፈፃፀም ደረጃ የፅሁፍ ሪፖርት ተቀብሎ ተገቢውን ግብረ መልስና ድጋፍ ይሰጣል፡፡

   ሐ) በየሳምንቱ ከወረዳ ሴቶች ሊግ ጋር የስልክ ልውውጥ በማድረግ ኢንፎርሜሽን ይቀበላል

   መ) አመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማና የቀጣይ አመት እቅድ ለወረዳ ሴቶች ሊግ አመራር ኦሪንቴሽን ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 42. የአዲስ አበባ ከተማ የወረዳ/ድሬደዋ ቀበሌ የብልጽግና ፓርቲ ሴት ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ሴት ሊግ አሰተባባሪ ኮሚቴ አመራር ከወረዳዉ/ቀቤሌው ሴት ሊግ ኮንፍራንስ የሚመረጥ/የሚወከል 7 አባላት ያሉት ኮሚቴ ሆኖ ከመሀከላቸው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣሉ፡ ፡ የወረዳው ሴት ሊግ ጽ/ቤት አመራር አባላት በኮንፍራንሱ ካልተመረጡ የአስተባባሪ ኮሚቴ መድረክ ተሳታፊዎች ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 43. የአዲስ አበባ ከተማ የወረዳ/የድሬደዋ ቀበሌ የብልጽና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊ

1. የሊጉ የፖለቲካ ስራና የሴቶች የእለት ተእለት እንቅስቃሴ አጠቃላይ ሁኔታ ይከታተላል፣ ይመራል፣
2. የክፍለ ከተማዉ ሴቶች ሊግ ያወጣውን እቅድ መነሻ በማድረግ እንደወረዳው/ቀበሌው ተጨባጥ ሁኔታ የራሱን ዕቅድ ያቅዳል ያስፈጽማል፡፡
3. በወረዳ/በቀበሌ የሚካሄዱ የሊጉ፣ፓርቲና የመንግስት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ሴቶችን ማሳተፍ መቻላቸውን ይከታተላል፣ ይመራል፣

4. የሊጉ፣ የፓርቲና የመንግስት ሴት አመራር አካላትን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልእኳቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ የማብቃት ስራ ይሰራል፡፡
5. ስለ ስራው ክንውን ቀጥሎ ላለው የሴት ሊጉ አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
6. አዲስ አበባ ለክፍለ ከተማ ሴቶች ሊግ እና ድሬደዋ ተጠሪነቱ ለአስተዳደሩ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡ ሌሎች ከተሞች ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ተጠሪነት ተጠሪ ለሆኑበት መዋቅር ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 44. የአዲስ አበባ ከተማ የወረዳ/የድሬደዋ አስተዳደር ቀበሌ የብልጽግና ፓርቲ ሴት ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር፣

1. የሊጉው አስተባባሪ ኮሚቴ ሳምንታዊ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡
2. ምልአተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 45. የወረዳ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የወረዳ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ኃላፊ ...................................................... ሰብሳቢ
2. የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ........................................ ም/ሰብሳቢ
3. የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ........................................... አባል

## አንቀጽ 46. የወረዳ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የሴቶች የፖለቲካ፣ የአደረጃጀትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ከክፍለ ሴቶች ሊግ የሚወርዱ እቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ወረዳ/ቀበሌ ከሴቶች ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል፣
3. በወረዳው/ቀበሌ የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የሊጉንና ፓርቲ ስራዎችን ከመተግበር አኳያ በሴቶች ዙሪያ ያሉ መልካም ልምዶችን በመለየትና በመቀመር እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡

4. የሊጉን አባላት የእለት ተእለት ግንባታ ስራን እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የሊጉን አባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የሊጉ ህዋስና የመሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል ተግባራዊ መሆኑም ያረጋግጣል፡፡
5. በሊጉ የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር የስልጠና ስራ ያጠናል፣ ያቅዳል፣ ያደራጃል ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡
6. የስራ እቅዶችና አፈጻጸሙን በሚዲያና በህዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለህዝብ ያስተዋውቃሉ፡፡
7. በሊጉ ልሳንና በወርዱ ጽሁፎች ላይ በሚካሄዱት ውይይቶች የሴት አባላት የአቅም ግንባታ ስራዎችን ይመራል፣
8. ተጠሪነቱ ለወረዳ/ለቀበሌ ሴቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ እና ክፍለ ከተማ/አስተዳደሩ የሊግ ጽ/ቤት ኮሚቴ ይሆናል፣

## አንቀጽ 47. የወረዳ/የቀበሌ ብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. የሴት ሊጉ ጽ/ቤት ሳምንታዊ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
2. ምልዓተ ጉባዔው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምጽ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምጽ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡
4. የሴት ሊግ መሰረታዊ ድርጅቶችና ህዋሳትን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ቀጥሎ ላለው የሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ሪፖርት ይልካል፡፡
   ሀ. በየወሩ የሴት ሊጉ መሰረታዊ ድርጅቶችና ህዋሳት ያሉበት አፈፃፀም ደረጃ የፅሁፍ ሪፖርት ተቀብሎ ተገቢውን ግብረ-መልስና ድጋፍ ይሰጣል፡፡
   ለ. የሩብ ዓመት ተግባራት ይገመግማል፡፡
   ሐ. አመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማና ቀጣይ አመት ዕቅድ ለሚመለከታቸው አካላት ኦሬንቴሽን ይሰጣል፡፡

# ክፍል አምስት

## በየደረጃው የሚኖር የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ ኮንፈረንስ ውክልና፣

**አንቀፅ 48. በብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 23 (4) መሰረት በየደረጃው የሊጉ ኮንፈረንሶች የሚዋቀሩ እንዲሁም በአንቀፅ 25 እና 26 መሰረት ተግባርና ኃላፊነታቸውን የሚከውኑ ሆኖ፤ ለዚሁ ተግባራዊነት ኮንፈረንሶቹ በሚከተለው አግባብ በየደረጃው በሚኖር ውክልና ይመሰረታሉ፡-**

1. የክልል፤ የዞን፤ የወረዳ/ልዩ ወረዳ፤ የከተማ እና ቀበሌ የሊግ ኮንፍራንሶች ውክልናና ስብጥር በሴቶችና በአባላት ብዛት ይወሰናል፤
2. እያንዳንዱ አደረጃጀት የሴቶችና የአባላት ብዛትን መሰረት በማድረግ በሚሰጠዉ ኮታ ላይ ተመስርቶ በየአደረጃጀቱ በአባላት ቀጥተኛ ተሳትፎ በሚካሄድ ምርጫ የሴቶች ሊግ ኮንፈረንስ ተሳታፊዎቹን የሚወክል ይሆናል፣
3. ለክልል ሴቶች ሊግ ኮንፍራንስ እንደ ክልል አባላት ብዛት ከ300 አስከ 1500 አባላት ይሳተፋሉ፤
4. በዞን ደረጃ እንደ ሴቶች ሊግ አባላት ብዛት ከ300 እስከ 1000 አባላት ይሳተፋሉ፤
5. ልዩ ወረዳ ፤ ወረዳዎቸና ከተሞች እንደ ሴቶች ሊግ አባላት ብዛት ከ200 እስከ 1000 አባላት ይሳተፋሉ፤
6. በቀበሌ ደረጃ/በመሰረታዊ ድርጅት ደረጃ ያሉ ሁሉም አባላት በኮንፈረንሱ እዲሳተፉ ይደረጋል

# ክፍል ስድስት

## የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ የመሰረታዊ ድርጅትና የሕዋሳት አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

**አንቀጽ 49. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት አደረጃጀት**

1. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት በክልል፣ በዞን፣ ከተማ፣ ወረዳና በቀበሌ ውስጥ የሚገኙ የሴቶች ሊግ አባላትን የያዘ ሁለትና ከዛ በላይ የሆኑ የሊጉ ህዋሳትን በመያዝ የሚደራጁ ሆኖ፡-

   ሀ. የመንግስት ሰራተኞች /ለክልል፣ ዞን/ልዩ ወረዳ፣ ከተማ፣ ወረዳና ቀበሌ መስርያ ቤቶች/ የሚሰሩ በየዘርፉ ማለትም የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊ መሰረታዊ ድርጅቶች የሚቋቋሙ

ሆኖ፣ ተጠሪነታቸው በየደረጃው ላለ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ወይም ለሚዋቀረው አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

ለ. ሴቶች ሊግ አባል የሆኑ መምህራን፣ የአስተዳደር ሰራተኞች እና ተማሪዎች መሰረታዊ ድርጅት በተቋም ወይም በወረዳ፣ በቀበሌ (ለድሬዳዋ) የሚደራጅ ሆኖ ተጠሪነቱ ለሚገኝበት ቀበሌ (ለድሬዳዋ) ወይም ወረዳ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

መ. በሆስፒታል የሚሰሩ የሴቶች ሊግ አባላት መሰረታዊ ድርጅት በተቋማቸው የሚቋቋም ሆኖ ተጠሪነቱ ለከተማ (አዲስ አበባ ክ/ከተማ) ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

ሠ. የገጠር አርብቶና አርሶ አደሮች አደረጃጀት፣ የገጠር ባለሞያዎች በአንድ የሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ይደራጃሉ፡፡ ተጠሪነታቸው ለወረዳቸው ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

ረ. የከተማ ነዋሪዎች መሰረታዊ ድርጅቶች በመኖሪያ ለከተማቸው/ወረዳ የሚደራጁ ሲሆን፣ ተጠሪነታቸውም ለከተማቸው/ወረዳ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

ሰ. በአንድ ዘርፍ የተሰማሩ ወይም አንድ አካባቢ ተደራጅተው የሚሰሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ቁጥራቸው በቂ ከሆነ በአንድ የሴቶቸ ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ታቅፈው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ቁጥራቸው አነስተኛ ከሆነ ተመሳሳይ ባህርይ ያላቸው በክላስተር ይደራጃሉ፡፡ ተጠሪነታቸው ለከተማቸው ወይም ወረዳ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

ሸ. የላብ አደሮች ሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት በሚሰሩባቸው ተቋማት ወይም በኢንዱስትሪ ክላስተር የሚቋቋሙ ሆነው፣ ተጠሪነታቸው ለከተማቸው/ወረዳ ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡

2. በየትኛውም ደረጃ የሚቋቋሙ ሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅቶች ሁለት ህዋሳት ያሉት ሆኖ ከ14 አባላት ጀምሮ ይሆናል፡፡ የአባላት ቁጥር ባነሰባቸው አካላት ቁጥራቸው እስከሚጨምር ድረስ ተመሳሳይ ባህሪና የቦታ ቅርበት ያላቸው በአንድ መሰረታዊ ድርጅት መደራጀት ይችላሉ፡፡
3. እያንዳንዱ መሰረታዊ ድርጅት 12 አባላት ባሉት የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ይመራል፡ ፡ አመራሩም በመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ ይመረጣል፡፡
4. የሚመረጡት የአመራር አባላት የሚከተሉትን መሰረታዊ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. በተሰማራችበት የስራ መስክ ባስመዘገበችው የስራ ውጤት ለሌሎች አርአያ የሆነች፣

ለ. በሙያዋና በስነ-ምግባሯ ምስጉን የሆነችና የተሰጣትን ተልዕኮ በብቃት የምትወጣ፣

ሐ. ለውጡን ወደፊት ይዛ የመሄድ ራዕይ ያላት አባል ፣

መ. የሴቶች ሊግ እና የፓርቲውን አሰራሮች በማወቅና ተግባራዊ በማድረግ የተሻለ እንቅስቃሴ የምታደርግ ፣

ሠ. በተሰማራችበት ስራ ሳትወሰን ለሴቶች ሁለተናዊ ተጠቃሚነት የልማትና የመልካም አስተዳደር እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረከተች፣

ረ. በአካባቢው ሕብረተሰብና የስራ ጓደኞቿ ዘንድ በስርዓቷና በማሕበራዊ ግንኙነቷ የተሻለ ተቀባይነት ያተረፈች፣

ሸ. የመሰረታዊ ድርጅቱ አመራር አባላት አስከተቻለ ድረስ ከልዩ ልዩ ህዋሳት አባላት መካከል እንዲመረጡ ይደረጋል፡፡

ቀ. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ የራሱን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ ፀሀፊና ገንዘብ ያዥ ይመረጣል፡፡ በስሩም የሚከተሉት ንዑሳን ኮሚቴዎች ይኖሩታል፡ ፡

ሀ. የፖለቲካ ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ

ለ. የአደረጃጀት ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ

ሐ. የፋይናንስ ንኡስ ኮሚቴ

## አንቀፅ 50. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ተልዕኮ፡-

1. በሚኖሩበት አካባቢ ውስጥ የሚካሄዱትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ጉዳዮች፣ የመልካም አስተዳደርና የሰላም ተግባራት በብቃት እንዲያንቀሳቀሱ የሴቶች ሊግ አባላትን ማብቃት፡
2. የሴቶች ሊግ አባላትና የሴት አመራር አካላት ፖለቲካዊና ስነ-ምግባራዊ ብቃት ማጎልበቻ፣ የተሞክሮ መለዋወጫ መድረክ ሆኖ ማገልገል፡፡
3. በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና በፖለቲካ ስራዎች ያሉትን መልካም ልምዶች በእያንዳንዱ የሴት ሊግ አባል በተሟላ መልኩ ማስፋፋት፡፡
4. በማያቋርጥ አኳኋን የአዳዲስ የሴት ሊግ አባላት ምልመላ እንዲካሄድ ተገቢውን አመራርና ድጋፍ ይሰጣል፣ አባላት ጠንካራ ፖለቲካዊ ህይወት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

## አንቀፅ 51. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የብልጽግና ፓርቲ በሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ የፀደቀውን ዕቅድ ዝርዝር አፈፃፀም በማዘጋጀት ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣
2. በልማት፣ በመልካም አስተዳደር በአደረጃጀትና በፖለቲካ ስራዎች የሴቶች ተጠቃሚነት መረጋገጡን እና ያሉትን መልካም ልምዶች በእያንዳንዱ ሴቶች ሊግ አባልና መዋቅራቸው ደረጃ የማስፋት ስራ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት መከናወኑ ያረጋግጣል፣
3. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ ህዋስ አመራርን ፖለቲካዊና የአመራር አቅም በሴሚናሮችና በግምገማ ነክ ስልጠናዎች በቀጣይነት የመገንባት ስራ ይሰራል፣
4. የንዑሳን ኮሚቴዎችን እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ አመራር ይሰጣል፣
5. የሊጉን ህዋሳት ውይይት አፈፃፀምን ይከታተላል፡፡ በውይይቱ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በመለየት እንዲሰራበት ያደርጋል፡፡ ፈጣንና ውጤታማ የግብረ መልስ ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣
6. በስሩ የተደራጁ ህዋሳት ጠንካራ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ አስፈላጊውን አመራር ይሰጣል፡፡

7. አጠቃላይ አባላት ተልእኮአቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል፣ በዚህ ረገድ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፡፡
8. በሴቶች ሊግ መተዳደርያ ደንብ መሰረት ለመሰረታዊ ድርጅት የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች ያከናውናል፤ መተዳደርያ ደንቡ በሚሰጠው ስልጣን ክልልም የአባላትን ቅጣት ይወስናል፡፡
9. ለሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ በየሦስት ወሩ፣ አንድ እርከን ቀጥሎ ላለው ሊግ ጽ/ቤት ወይም ለኮሚቴ በየወሩ የተከናወነውን ፖለቲካዊና አደረጃጀት እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
10. የአባላትን ማህደር በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፡፡
11. ለሰቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶን ያከናውናል፡፡
12. የአባላት መዋጮ በደረሰኝ ሰብስቦ ለሚመለከተው ክፍል ገቢ ያደርጋል፡፡
13. ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስና በየደረጃው ላለው ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ወይም ለሚዋቀረው ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 52. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

1. የሴቶችን ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራ ትመራለች ፣ ታስተባብራለች፡፡
2. የሴቶች ሊግ ህዋስ አመራር ፖለቲካዊ አቅም ግንባታ ስራን ትከታተላለች፣ በበላይነት ትመራለች፡
:
3. የሊጉ ህዋሳት ጠንካራ የተደራጁ ሆነው እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ትከታተላለች ታረጋግጣለች
::
4. የአመራር ኮሚቴውንና የመሰረታዊ ድርጅቱን ኮንፈረንስና አስቸኳይ ስብሰባዎች በሰብሳቢነት ትመራለች፡፡
5. ለስብሰባዎቹ የሚሆን የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ወዘተ… ታዘጋጃለች ወይም የሚመለከታቸው ኮሚቴዎች እንዲያዘጋጁ በማድረግ ለስብሰባው ታቀርባለች፡፡
6. ከበላይ አካል ጋር ኮሚቴውን በመወከል ትገናኛለች፡፡ ለበላይ አካል ሪፖርት ታቀርባለች፡፡ ከበላይ አካል መመሪያ ትቀበላለች፡፡
7. ተጠሪነቷ ለመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴና ለየመዋቅራቸው ሴቶች ሊግ ጽ/ቤ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 53. የምክትል ሰብሳቢዋ ተግባርና ኃላፊነት

1. ሰብሳቢዋ በማትኖርበት ጊዜ ተክታ ትሰራለች፣
2. በፖለቲካ ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ የተቀመጡ ስራዎችን በበላይነት ትመራለች ታስተባብራለች፡፡
3. ከሰብሳቢዋ የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ታከናውናለች፡፡
4. ተጠሪነቷ ለሰብሳቢዋና ለፖለቲካ ኃላፊዋ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 54. የፀሐፊዋ ተግባርና ኃላፊነት

1. ለአደረጃጀት ንኡስ ኮሚቴ የተቀመጡ ስራዎችን በበላይነት ትመራለች ኮሚቴውን ታስተባብራለች፡ ፡
2. የመሰረታዊ ድርጅቱና የአመራር ኮሚቴዎችን ሰነድ ትይዛለች፡፡
3. ከሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ታከናውናለች ፡፡
4. ተጠሪነቱ ለሰብሳቢዋ እና አደረጃጀት ኃላፊዋ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 55. ሴቶች ሊግ የፖለቲካ ሥራዎች ንኡስ ኮሚቴ አመራር አባላት አደረጃጀት

1. ንኡስ ኮሚቴው አራት የአመራር አባላት ሲኖሩት እነርሱም
   ሀ. የመሰረታዊ ድርጅቱ ምክትል ሰብሳቢዋ ............................ ሰብሳቢ
   ለ. አንድ የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል ............. ም/ሰብሳቢ
   ሐ. ሁለት የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል ............ አባል ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 56. የንኡስ ኮሚቴው ዋና ዋና ተግባራት

1. በዚህ ንኡስ ኮሚቴ ውስጥ የአባላት ፖለቲካዊ የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራ፣ የስልጠና፣ ኮንፈረንስ፣ የአባላት ዓቅም ግንባታ ስራ፣ በልሳናትና በብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ መፅሔት ላይ የሚደረግ ውይይት ይመራል፣
   ሀ. እያንዳንዷ የሴት ሊግ አባል ብቁ ፖለቲካዊ ግንዛቤና አቋም ኖሮአቸው ተልእኮዎቹን ለመፈፀም የሚያስችላቸው ሁኔታ ላይ እንዲገኙ ተከታታይ ውይይትና ተግባር ውስጥ እንዲገባ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ፣
   ለ. እያንዳንዱ አባልና አመራር መልካም ልምዶችን ለማስፋፋትና ለመተግበር የሚያስችላቸው የአስተሳሰብ ዝግጁነት እንዲኖራቸው ይሰራሉ፣
2. የህዋስና የመሰረታዊ ድርጅት አመራሮች አቅም ግንባታ ስራ እንዲሰራ ያደርጋሉ፣
   ሀ. የፖለቲካ ስራ ዘርፍ በሚያወጣው እቅድ መሰረት መከናወኑን ይከታተላሉ፡፡
   ለ. የተገኘውን ውጤትና የሚታዩ ችግሮችን በመከታተል ይገመግማሉ፣ መፍትሔ እንዲሰጥ ያደርጋሉ፡፡
3. አባላት በልሳናት አና በብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ መፅሔት ላይ ውይይት እንዲያካሂዱ ማድረግ፡ ፡
   ሀ. ለሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት አባላት መወያያ የሚሆኑ በልሳናትና በብልፅግና ሴቶች ሊግ መፅሔት ፅሁፎችን እቅድ ያዘጋጃል፡፡

ለ. በእቅዱ መሰረት ልሳናት በወቅቱ የሚመጡበትን ስርዓት ይዘረጋል በዚሁ መሰረት መድረሳቸውን ያረጋግጣል፣

ሐ. የህዋሳት የውይይት ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ በፕሮግራማቸው መሰረት ውይይት ማካሄዳቸውን ይከታተላል፡፡

መ. በህዋሳት ውይይት ላይ የተነሱ ጉዳዮችን ከህዋሳት የፖለቲካ ስራ ሃላፊዎች በመቀበል ምላሽ ይሰጣል፡፡

ረ. ከንኡስ ኮሚቴው አቅም በላይ የሆነውን ለመሰረታዊ ድርጅት አመራርና ለፖለቲካ ስራ ዘርፍ በማቅረብ አቅጣጫ ይቀበላል፣ ለህዋሳት ያሳውቃል፡፡

4. በመሰረታዊ ድርጅት ደረጃ ኮንፈረንስ እንዲካሄድ በማድረግ አባላት በኮንፈረንስ መድረኮች ላይ ተገኝተው በሚገባ መወያየታቸውንና ግንዛቤ መያዛቸውን ይከታተላል፣

5. የተለያዩ ሴሚናሮች ለሴቶች ሊግ አባላት እንዲሰጡ ማድረግ፣

ሀ. የመወያያ ርእሶችንና ሰነዶች በወቅቱ መድረሳቸውን እንዲሁም አወያዮች መሟላታቸውን ይከታተላል፣

ለ. በበላይ አካል በሚሰጠው እቅድ መሰረት አባላት በተሟላ መልኩ በሴሚናሮች ላይ መሳተፋቸውንና በቂ ፖለቲካዊ ግንዛቤ ማዳበራቸውን ይከታተላል፣

6. ስልጠናዎች እንዲሰጡ ማድረግ፡-

ሀ. የሚካሄዱ ስልጠናዎችን ያደራጃል፣

ለ. በበላይ አካል የሚካሄዱ ስልጠናዎች ሲኖሩ የምልመላና የሰው ሃይል ዝግጅት ስራዎችን ያከናውናል፣

ሐ. የተሰጡ ስልጠናዎችን ውጤት ተከታትሎ ይገመግማል፣ ክፍተቶችን ይለያል፣ ሪፖርት ያቀርባል፣

መ. ወደፊት ሊሰጡ ስለሚገባቸው ስልጠናዎች ለሊጉ መሰረታዊ ድርጅት አመራር ሃሳብ ያቀርባል፣

7. ከፖለቲካ ኮሚቴ ጋር የስራ ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍ ያገኛል፣ ሪፖርትም ያቀርባል፡፡ የንኡስ ኮሚቴውን ስራ በተመለከተ ከፖለቲካ ኮሚቴ ጋር እየተገናኘ አስፈላጊውን የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፣ ድጋፍ ያገኛል፣

8. ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢና ለፖለቲካ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 57. የአደረጃጀት ስራዎች የንኡስ ኮሚቴ አደረጃጀትና አሰራር

1. ኮሚቴው አራት የአመራር አባላት ሲኖሩት እነሱም፡-

ሀ. የመሰረታዊ ድርጅቱ ፀሀፊ ....................................... ሰብሳቢ

ለ. አንድ የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል .......... ምክትል ሰብሳቢ

ሐ. ሁለት የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል ………. አባል ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 58. የአደረጃጀት ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ ዋና ዋና ተግባራት

የንኡስ ኮሚቴውን መረጃዎችና የአባላትን የግል ማህደር መያዝ፣ የአደረጃጀትና አሰራር መመሪያዎችን ተፈፃሚነት መከታተልና እያንዳንዱ አባል በአደረጃት ታቅፎ ተልዕኮዎቹን እየፈፀመ መሆኑን፣ አዳዲስ የአፈፃፀም ልምዶችን መቀመርና ወደ ሌሎች የማስፋፋት ስራ ይሰራል፡፡

የአደረጃጀት ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. አባሉ የተደራጀና ጠንካራ አደረጃጀት ሆኖ ተልዕኮዎቹን የሚወጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስራ ማቀድና ማከናወን፣
   ሀ. እያንዳንዱ አባል በተለይም የመሰረታዊ ድርጅትና የሕዋስ አመራር በተልዕኮው ላይ ግልፅ የሆነ፣ ፖለቲካዊ ግንዛቤው ከፍ ያለና ጠንካራ አቋም ያለው፣ በተግባር ራሱ ሰርቶና ተጠቅሞ ለሌሎች በአስተማሪነቱ የሚጠቀስ እንዲሆን ያደርጋል፣
   ለ. አባላችን የተደራጀና እንደ አንድ ተልዕኮ ፈፃሚ ኃይል ጠንካራ ተጽዕኖ እያሳረፈና ለውጥ እያመጣ መሆኑን ማረጋገጥ፣
   ሐ. አባሉ ተደራጅቶ ወደ ስራ ለመግባትና የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት ያሉበትን ችግሮች በየጊዜው እየገመገመ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
2. የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያዎች በአባላት ታውቀው ስራ ላይ እንዲውሉ የሚያስችል ዲስፕሊን መፍጠር፣
   ሀ. አባላት በአደረጃጀትና አሰራር መመሪያዎች ላይ በቂ ግልጽነት የያዙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ ካልያዙ ስልጠና እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
   ለ. የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ችግሮች ካሉ ያስተካክላል፡፡
3. የሴቶች ሊግ አባላት አደረጃጀት መፍጠርና ማጠናከር
   ሀ. ሁሉም ሊግ አባላት በመሰረታዊ ድርጅትና በህዋስ አደረጃጀቶች ውስጥ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፣
   ለ. አደረጃጀቶቹ የአባላትን ግንዛቤ በማሳደግና ተግባራዊ እንቅስቃሴያቸውን በመምራት በኩል ወሳኝ ሚና እንዳላቸው በትክክል እንዲገነዘቡ ያደርጋል፣
   ሐ. አባላት ሚናቸውን እየተጫወቱ መሆናቸውን መከታተልና ማረጋገጥ፣ ለሚታዩ ችግሮችም መፍትሄ ያፈላልጋል፣
4. እያንዳንዱ አባል ተልዕኮዎቹን ስራ ላይ ማዋሉን ክትትል በማድረግ የእያንዳንዷን አባል ደረጃ መለየት፣ ድጋፍ ማድረግ፣

ሀ. እያንዳንዷ አባል ተልዕኮዎቹን በግልጽ መያዟን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

ለ. በዚሁ መሰረት ስራ ላይ ማዋሉን በጥብቅ ክትትል ይለያል፣

ሐ. በለውጡ አፈፃፀም ውጤቱ ላይ በመመስረት በየጊዜው ለእያንዳንዷ አባል ደረጃ እንዲወጣለት ያደርጋል፣

መ. አባሏ ግንባር ቀደም ሚናዋን ስለመወጣቷም በአባላት እንዲመዘንና የማጠናከሪያ ድጋፍ ይሰጣል፣

ሠ. ግንባር ቀደም ሚናቸውን የማይወጡ ካሉ ተገቢውን ማስተካከያ ያደርጋል፣

5. የሴቶች ሊግ አባላት ማህደር በየጊዜው እየተሞላ መያዙን ማረጋገጥ

ሀ. እያንዳንዱ አባል የግል ማህደር የተዘጋጀለት መሆኑን ያረጋግጣል፣

ለ. በየ6 ወሩ በሂስና ግለሂስ ላይ የተመሰረተ የታደሰ ማህደር መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣ የአባሏ የግል ማህደር ለተፈላጊ ስራ እንዲውል ያደርጋል።

6. ከአደረጃጀት ኮሚቴ ጋር የስራ ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍ ያገኛል፣ ሪፖርትም ያቀርባል፤ የንኡስ ኮሚቴውን ስራ በተመለከተ ከአደረጃጀት ጋር በየጊዜው እየተገናኘ አስፈላጊውን የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ድጋፍ ያገኛል፣

7. ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢና ለአደረጃጀት ኮሚቴ ይሆናል፣

## አንቀጽ 59 ሴቶች ሊግ ፋይናንስ ንኡስ ኮሚቴ

1. የንኡስ ኮሚቴው አባላት ቁጥር ሶስት ሆኖ በሊጉ የገቢ እቅድ ማዘጋጀት፣ ገቢ ማሰባሰብና ማስገባት ዙሪያ የስራ ክፍፍል ይኖራቸዋል።
2. የሊጉንን አመታዊ ገቢ ዕቅድ ማዘጋጀት እና በእቅዱ መሰረት ማሰባሰብ፣
3. የሊጉ ገቢዎች በህጋዊ ደረሰኝ መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል ሪፖርት ለሊግ ጽ/ቤት ያደርጋል፣
4. የልሳናትና የሊጉ መፅሔት የመፅሄት ሽያጭ ገቢ ያደርጋል፣
5. ከብልፅግና ፓርቲ የፋይናንስ ንኡስ ኮሚቴ ጋር ተቀናጅቶ ይስራል
6. ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢና ለሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል።

## አንቀጽ 60. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት አሰራር

1. የሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ ያደርጋል፣
2. የሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ የለውጥ ሂደት ያለበት ደረጃ በቁልፍ አጀንዳነት ተይዞ ይገመገማል፣
3. የኮንፈረንስ ጊዜ ቢያንስ ከ1 ወር በፊት አስቀድሞ እንዲታወቅ ይደረጋል። በተቻለ መጠን ኮንፈረንሱን ተከታታይ የሆኑ የበአል ቀናትን ግምት ውስጥ በማስገባት እንዲጠራ ማድረግ ያስፈልጋል።

4. የመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ በየሶስት ወሩ የሚካሄድ ይሆናል፣
5. የኮንፈረንስ አጀንዳዎች ምን ሊሆኑ እንደሚገባ ተመካክሮ ለህዋሳት ማሳወቅና ህዋሳት የሚፈልጉት አጀንዳ ካለ እንዲጠቀሙ ማድረግ ይኖርበታል፣
6. ልዩ ልዩ ንኡሳን ኮሚቴዎች የስራ አፈፃፀማቸውን በተመለከተ የየራሳቸውን ሪፖርት በአጭሩ እንዲያዘጋጁና በሪፖርቱ የቀጣይ እቅድም መነሻዎች እንዲቀርቡ ይደረጋል።
7. ከበላይ አካል በኮንፈረንሱ ላይ ቢታዩ ይጠቅማሉ የሚባሉ አጀንዳዎችን በመቀበል ከየመዋቅራቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ለውይይት እንዲቀርቡ ይደረጋል፣
8. በኮንፈረንስ መድረክ ላይ አጀንዳዎችን በማፅደቅ በቅደም ተከተል ውይይት ይደረግባቸዋል፣
9. አባላት በየርዕሱ ነፃ ሆነው ሀሳባቸውን እንዲገልፁ፣ እንዲቃወሙም ሆነ እንዲደግፉ ሰፊ እድል መስጠትና በበቂ ሁኔታ ከተወያዩ በኋላ ወደ ውሳኔ ሃሳብ የማምራት አግባብን መከተል ይገባል፣
10. የውሳኔ ሃሳቡ በፅሁፍ ተዘጋጅቶ በንባብ እንዲቀርብና በድምፅ እንዲወሰን ይደረጋል፣
11. በኮንፈረንሱ ማጠቃለያ ላይ የጋራ የአቋም መግለጫ ማውጣት፣ የአቋም መግለጫው ሁሉንም የውሳኔ ሃሳቦች በአጭር በአጭሩ እንዲይዝ በማድረግ ለህዋሳት ሃላፊዎች ኮፒ እንዲደርስ ማድረግ ይገባል፣
12. በኮንፈረንሱ ማጠቃለያ ላይ የአመራሩ ሂስና ግለሂስ ሪፖርት ለአባሉ እንዲቀርብና የሚጨመር ወይም የሚስተካከል ካለ እንዲስተካከል ይደረጋል፣
13. የአመራር ምርጫ በየአመቱ መጀመሪያ በሚካሄደው ኮንፈረንስ ይሆናል፣
14. አባላት ወይም የበላይ አካል አስቸኳይ ኮንፈረንስ ሲጠይቁ ለመላ አባላት ህዋሳት ስብሰባ ላይ አሳውቆ ግማሽ ያህሉ ከደገፈው እንዲካሄድ ይደረጋል፣
15. የኮንፈረንሱ አጠቃላይ ሂደት በቃለ-ጉባኤ እንዲያዝ ይደረገል፣
16. የኮንፈረንሱ ምልአተ ጉባዔ ከመሰረታዊ ድርጅቱ አባላት ከግማሽ በላይ /50%+1/ ሲገኙ ይሆናል፣
17. ኮንፈረንሱ በድምፅ ብልጫ የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች በኮንፈረንሱ ከተገኙት ውስጥ ከግማሽ በላይ /50%+1/ የደገፉት ሊሆን ይገባል።

## አንቀጽ 61. በኮንፈረንሱ ውሳኔዎች መሰረት ተግባርን መምራት

1. ኮንፈረንሱ ከተጠናቀቀ በኋላ አመራሩና መላ አባላት በየአደረጃጀታቸው አማካይነት ፈጥነው ወደ ስራ መግባትና የተቀመጡትን ተግባራት ለማስፈፀምና ግቡን ለማሳካት መረባረብ ይገባቸዋል፣
2. የጋራ ስራዎችን በስምምነታቸው መሰረት በከፍተኛ የሃላፊነት መንፈስ ይፈፅማሉ፣
3. የመልካም አስተዳደርና ሌሎች ተግባራትን በእቅዱ መሰረት መፈፀም፣
4. ከእያንዳንዱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ብቁ ትምህርት መውሰድ፣ በአመራር ደረጃ ምርጥ የአባላት ልምዶችን እየለቀሙ ለሁሉም ማሳወቅና የአፈፃፀም ስልቶች የጋራ ሃብት እንዲሆኑ ማድረግ፣

5. የስራ አፈፃፀም ሂደቱን በተቀመጡ ጊዜዎች በመደበኛነት መገምገምና አስፈላጊውን የእቅድ ማስተካከያ እያደረጉ ስራውን በጥራት መስፈፀም ይጠበቅባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 62. በሴቶች ሊግ አመራር ደረጃ የመማማር አሰራርን በጥቅም ላይ ማዋል

1. አመራሩ የስራ አፈፃፀሙን መሰረት በማድረግ መማማር ፕሮግራም በየወሩ ያካሂዳል፣
2. በየሶስት ወሩ በተራ ቁጥር 1 የደረሰበትን ውጤት ለሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት በአጭሩ አቅርቦ ያስገመግማል፡፡ ከሴቶች ሊግ አባላት የሚቀርቡ ትችቶች ካሉ ተቀብሎ ምላሽ ይሰጣል፣
3. በሁሉም ደረጃ የሚካሄደው መማማር ፕሮግራም ገንቢና በተጨባጭ ድክመቶች ላይ የተመሰረተ፣ ስራን እንጂ ሰውን ማእከል ያላደረገ እንዲሆን ይደረጋል፣

## አንቀጽ 63. የሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት አመራሮች አሰራር

የአመራር ኮሚቴ ስብሰባና ግንኙነት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

1. አመራር ኮሚቴው በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡ በዚህ መሰረት፡-
   ሀ. ከህዋስና ከንዑሳን ኮሚቴ የመጣለትን ሪፖርት፣ እንዲሁም ከበላይ አካል የሚወርድለትን እቅድና አቅጣጫ ላይ ውይይት ያደርጋል፣ ለህዋሳትና ለንዑሳን ኮሚቴ አቅጣጫ ይሰጣል፣
2. አመራር ኮሚቴው በሁሉም ጉዳዮች ላይ ያለውን ሃሳብ ለህዋሳት በአፋጣኝ ያሳውቃል፣

## አንቀጽ 64. የንኡሳን ኮሚቴዎች አሰራር

1. ሁሉም ንዑሳን ኮሚቴዎች በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ይኖራቸዋል፣
2. በስብሰባው ያለፈውን የስራ አፈፃፀም ይገመግማሉ፣ የቀጣይ 15 ቀናት የስራ እቅድ በማፅደቅ ስራዎችን ተከፋፍለው ስምሪት ያደርጋሉ፣
3. ለመሰረታዊ ድርጅት የሚቀርብ ሪፖርት ያዘጋጃሉ፣ ያቀርባሉ፣
4. ለህዋሳት ኮሚቴ አቅጣጫዎችን ያወርዳል፣

## አንቀጽ 65. የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ከሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ኮሚቴ ጋር የሚኖረው ግንኙነት

1. ሰብሳቢዋ ከሊግ ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር እና ከኮሚቴ ሰብሳቢ ጋር የስራ ግንኙነት ታደርጋለች፣
2. የሊግ ጽ/ቤት ወይም ኮሚቴ አመራሩ በ3 ወር አንድ ጊዜ የሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ፣ ፀሀፊና የፋይናንስ ሀላፊ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢዎችን አንድ ላይ ወደ ማእከል በመጥራት የስራ ግምገማ ይደረጋል፡፡ የዚህ ግንኙነት ዝርዝር አተገባበር ስለአመራር የግንኙነት ከላይ በተገለፀውና ውስጥ በሰፈረው አግባብ መሰረት ይፈፀማል፣

3. እንደየአስፈላጊነቱ በየደረጃው ያሉት የሊግ ጽ/ቤት ፖለቲካና አደረጃጀት ኃላፊዎች ከመሰረታዊ ድርጅት አመራር አባላት ጋር መደበኛ የስራ ግዚያቸውን በማይጋፋና ለነሱ አመቺ በሆነ ጊዜ የጋራ ስብሰባ ያደርጋሉ፣
4. ከበላይ አካል የሚሰጠውን እቅድና ልዩ ልዩ መመሪያ ቆጥሮ ይቀበላል፡፡ እቅዶችን ለተፈፃሚነት ያዘጋጃል፣
5. ለበላይ አመራር የሚቀርብ ትችት ካለው በዚህ መድረክ በመጠቀም ያቀርባል፣
6. በየሶስት ወሩ የተሟላ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ለሊግ ጽ/ቤት ወይም ለኮሚቴ ይልካል፣

## አንቀጽ 66. የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች የሴቶች ሊግ የህዋሳት አደረጃጀት

1. የሊጉ መሰረታዊ ድርጅት ለአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ የሚጠቀሙበት የህዋስ አደረጃጀት ይኖራቸዋል፡፡ የህዋስ አባላት ቁጥር ከ7-35 ይሆናል፣
2. የሊጉ ህዋሳት የሚመሰረቱት ሙሉ አባላትን በመያዝ በመኖሪያ አካባቢ እና በስራ ቦታ ሆኖ በሚከተለው መልኩ ይሆናል፣
   ሀ. የመንግስት ሰራተኞች /በፌደራል፣ በክልል፣ በዞን፣ በከተማ፣ በወረዳ/ልዩ ወረዳና በቀበሌ መስሪያ ቤቶች/ የሚሰሩ በተቋም ወይም በየዘርፉ ማለትም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊ ዘርፎችን መሰረት አድርገው ይደራጃሉ፣
   ለ. የመምህራን፣ አስተዳደር ሰራተኞችና የተማሪዎች ህዋስ አመቺ በሆነበት ቦታ /ተቋም፣ በወረዳ፣ በቀበሌ/ ደረጃ ይደራጃል፣
   መ. የሆስፒታል አባላት እንደ አመቺነቱ በሚሰሩበት ተቋም፣ ወረዳ/ቀበሌ ደረጃ ይደራጃሉ፣
   ረ. የገጠር አርብቶና አርሶ አደሮች ህዋሳት መንደር/ቀጠናን መሰረት በማድረግ ይደራጃሉ፡፡
   ሰ. በገጠር የተሰማሩ የመንግስት ሰራተኞች ህዋሳት የገጠር ባለሙያዎች እና በሌሎች ስራ የተሰማሩትን ባካተተ መልኩ የስራ ቦታ ወይም ቀበሌን መሰረት በማድረግ ይደራጃሉ፡፡
   ሸ. የከተማ ነዋሪዎች ህዋሳት የመኖርያ ቦታን መሰረት በማድረግ በቀበሌ፣ በመንደር፣ በቀጠና ወይም በወረዳ ደረጃ ይደራጃሉ፡፡
   ቀ. የከተማ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት አባላት በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ የሚደራጁ ሆኖ ቁጥራቸው አነስተኛ ከሆነ በአቅራቢያቸው ካለ ህዋስ ጋር ይደራጃሉ፡፡
   በ. የላብአደር አባላት በስራ ቦታቸው በሴቶች ሊግ ህዋስ ይደራጃሉ፡፡
   ተ. በክልል መንግስታት ወይም በህዝብ ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሚገኙ አባላት እንደ አመቺነቱ በሚኖሩበት ቀበሌ ወይም በአቅራቢያቸው ባሉ ተቋማት አደረጃጀቶች ውስጥ ታቅፈው በሴቶች ሊግ ህዋስ ያደራጃሉ፡፡
3. በአንድ ተቋም የሚሰሩ አባላት ቁጥራቸው ከሰባት በታች ከሆነ ከሌሎች ተቋም ጋር በክላስተር ይደራጃሉ፣

4. ሁሉም አባል በህዋስ ተደራጅቶ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል በአንድ የስራ ቦታ ወይም መኖሪያ የአባላት ቁጥር ከ35 በላይ ከሆነ ሌላ ህዋስ መደራጀት ይቻላል፣
5. እያንዳንዱ የሴቶች ሊግ ህዋስ የራሱን አመራር ኮሚቴ ይመርጣል እነዚህም፡-

   ሀ. ሰብሳቢ

   ለ. የፖለቲካ ኃላፊ

   ሐ. የአደረጃጀት ኃላፊ

   መ. የፋይናንስ ጉዳይ ይሆናሉ
6. ለሴቶች ሊግ ህዋስ አመራርነት የሚመረጡ አባላት የሚያሟሉት መመዘኛ ከላይ ለመሰረታዊ ድርጅት አመራርነት የሚመረጡ በደረጃው ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች ተመሳሳይ ይሆናል፡ ፡

## አንቀጽ 67. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ ህዋስ ተልዕኮ

1. አባላት በቀበሌያቸው/በወረዳቸው በመስርያ ቤታቸው ውስጥ በሚካሄዱ ብልፅግናን እና የሴቶችን እኩልነት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡና የሰላም ተግባራት ግንባር ቀደም ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ማብቃት በዚህ ሂደትም አባላትን በተግባር እንዲገነባ ይደረጋል፣
2. በህዋሱ ውስጥ የታቀፉትን አባላት በሙሉ በየግላቸው የሚያዘጋጁትን የግል እቅድ ማፅደቅ፣ አፈፃፀሙን መከታተል፣ መደገፍና ውጤቱን መገምገም፣
3. የአባላትን የፖለቲካዊና ድርጅታዊ ብቃት እንዲኖራቸው ይሰራል፣
4. የግንባር ቀደም ሴቶችን አዳዲስ አባላት በመመልመል የብልፅግና ፓርቲ አባል በማድረግ ወደ ሊጉ በመቀላቀል የተደራጀ ጠንካራ እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው ይደረጋል፣

## አንቀጽ 68. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ ህዋስ አሰራር

ህዋሶች የሚከተለው ውስጣዊ አሰራር ይኖራቸዋል፡፡

1. በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ይኖራቸዋል፣
2. የፖለቲካ ውይይት እና እያንዳንዱ አባል ብልፅግናን በሚያረጋግጡ ተግባራት ዙሪያ እንዲሁም የሴቶች እኩልነት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ዙሪያ በግንባር ቀደምነት የሚያደርገው እንቅስቃሴ፣ የአባላትና የጋራ አደረጃጀት፣ በአጠቃላይም የአባላት እንቅስቃሴ የሚገመገምበት ይሆናል፣
3. በግምገማው ላይ በመመስረትም የመማማር ፕሮግራም እንዲካሄድ ይደረጋል፣
4. የህዋስ ስብሰባ የሚካሄደው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ይሆናል፣
5. ማንኛውም አባል በህዋስ ስብሰባ የመገኘት ግዴታ አለበት፣ አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ምክንያት የማይገኝ አባል አስቀድሞ የህዋሱን ሰብሳቢ ማሳወቅና ማስፈቀድ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 69. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ ህዋሳት እንዲሁም የአመራር ኮሚቴና አባላት ተግባርና ኃላፊነት

1. የህዋስ አመራር ኮሚቴ የሚከተለው ተግባራት ይኖረዋል፡፡
   ሀ. የህዋሱን ሰብሳቢና ሌሎች ኃላፊዎች ይመርጣል፣
   ለ. የህዋስ አባላት በተግባርና በአስተሳሰብ ግንባር ቀደም ሆነው በመንቀሳቀስ ላይ መሆናቸውን ይከታተላል፣
   ሐ. ከመሰረታዊ ድርጅት የመጡ መመሪያዎችን የህዋሱ አባላት እንዲያውቋቸውና በአግባቡ እንዲፈፅሟቸው ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውንም ይቆጣጠራል፣
   መ. አባላት ተልእኮቻቸውን ከመፈፀም አኳያ ያሉበትን ሁኔታ ይገመግማል፣ እያንዳንዱን አባል ዕቅድ በመገምገም ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ውጤቱን ይገመግማል፣
   ሠ. አዳዲስ አባላት መስፈርቱን አሟልተው መመልመላቸውን ያረጋግጣል፣
   ረ. የህዋሱን የውይይትና የግምገማ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ በህዋሱ በማፅደቅም ስራ ላይ ይውላል፣
   ሰ. የህዋሱ የውይይት ፕሮግራም ሳይስተጓጎል የሚካሄድበትን ሁኔታ ለመፍጠር ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል፡፡ የሌሎችን ህዋሳት መልካም ተሞክሮ በመቅሰም ህዋሱ እንዲጠቀምበት ያደርጋል፣
   ሸ. አመራር ኮሚቴው በየ15 ቀኑ መደበኛ ስብሰባ በማድረግ መረጃዎችን ይለዋወጣል፣
   ቀ. ለሴቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት በየወሩ ሪፖርት ይልካል፣

2. **የህዋስ ሰብሳቢዋ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖራታል፡፡**
   ሀ. የህዋሱን ስብሰባ በሰብሳቢነት ትመራለች፣
   ለ. የህዋሱን ፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራ በበላይነት ታስተባብራለች፣
   ሐ. ህዋሱን በመወከል ከመሰረታዊ ድርጅት አመራር ጋር ትገናኛለች፣
   መ. ህዋሱ ጠንካራ የተደራጀ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ የሚያስችል አመራር ትሰጣለች፣
   ሠ. እያንዳንዱን የህዋስ አባል ፖለቲካዊ እንቅስቃሴውን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት ድጋፍ እንዲያገኝ ታደርጋለች፣

3. **የህዋሷ ፖለቲካ ኃላፊ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖራታል፡፡**

ሀ. የአባላትን ፖለቲካዊ ዝንባሌ ተከታትሎ በማወቅና ሪፖርት በማድረግ ተገቢውን ፖለቲካዊ ግንባታ እንዲያገኙ ታደርጋለች፣

ለ. እያንዳንዷ የሊግ አባል የማስፋት ስትራቴጂው ተሣታፊና ተጠቃሚ ከመሆን አኳያ ያለችበትን የግንዛቤና የቁርጠኝነት ሁኔታ በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ እንድታገኝ ታደርጋለች፤

ሐ. ህዋሳት እንዲወያዩበት ከበላይ አካል የሚሰጠውን አጀንዳ እየተከታተለች ህዋሱ እንዲወይይበት ታደርጋለች፤ አጀንዳውን በየርእሱ ከፋፍሎ ማቅረብ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለህዋሱ አባላት አጀንዳውን ታከፋፍላለች፣ የውይይት ኘሮግራም ታወጣለች::

መ. ከመሰረታዊ ድርጅት አመራር ጋር በመገናኘት ጋዜጣ በወቅቱ እንዲደርስ ታደርጋለች በወቅቱ ካልደረሰ ፈጥና ሪፖርት ታደርጋለች::

ሠ. የህዋስ አባላት ውይይትን ቃለ ጉባኤ ትይዛለች፤ በውይይቱ ወቅት የተነሱ አከራካሪና ልዩነት የተፈጠረባቸው፣ በሚገባ ያልተጨበጡና ማብራሪያ የሚሹ ሃሳቦችን መዝግባ ትይዛለች:: ረ. ለመሰረታዊ ድርጅቱ የፖለቲካ ሥራ ሃላፊ በየ15 ቀኑ ሪፖርት ታቀርባለች::

ሰ. ተጠሪነቷ ለህዋሱ ሰብሳቢ ይሆናል::

4. የአደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖራታል።
   ሀ. ህዋሷ ጠንካራ ሆና እንድትንቀሳቀስ የሚያስችል አመራር ትሰጣለች፣
   ለ. እያንዳዱ አባል በአደረጃጀትና አሰራር መመሪያዎች ላይ ያለውን ግንዛቤ ማጎልበትና በስራ ላይ እንዲይውል ትከታተላለች፣ አመራር ትሰጣለች፣
   ሐ. የህዋሱን አባላት ማህደር ትይዛለች፣ ሲያስፈልግም ለመሰረታዊ ድርጅቱ ታስተላልፋለች፣
   መ. የአባላት የመማማር ሂደት ቃለ-ጉባኤ ትይዛለች፣ ውጤቱን በእያንዳንዱ አባል ማህደር ታሰፍራለች፣
   ሠ. ለመሰረታዊ ድርጅት አደረጃት ኃላፊ በየወሩ ሪፖርት ታቀርባለች፣
   ረ ተጠሪነቷ ለህዋሷ ሰብሳቢና ለመሰረታዊ ድርጅቱ የአደረጃት ኃላፊ ይሆናል።
5. የህዋሷ ፋይናንስ ጉዳይ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖራታል።
   ሀ. የአባላትን መዋጮ ታቅዳለች፣ ከእናት - ርቲ ገንዘብ ያዠ ገር በመቀናጀት በህጋዊ ደረሰኝ እንዲሰባሰብ በማድረግ ለመሰረታዊ ድርጅት ሪፖርት ታደርጋለች፣
   ለ. የልሳናትና የብልፅግና ሴቶች ሊግ መፅሔት ሽያጭ ገንዘብ በማሰባሰብ ገቢ ታደርጋለች፣
   ሐ. ተጠሪነቷ ለህዋሷ ሰብሳቢና ለመሰረታዊ ድርጅት ፋይናንስ ኃላፊዋ ይሆናል፣

## አንቀጽ 70. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ የደጋፊዎች ቡድን አደረጃጀት

1. እያንዳንዷ የሊግ አባል በተሰማራችበት የስራ መስክ ይሁን መኖሪያ ቦታ በጋራ አብረው ለሚኖሩና ለሚሰሩ አካላት የፓርቲንና የሴቶች ሊግ ዓላማዎችና እንቅስቃሴ የማስረዳት ኃላፊነት ይኖርባታል:
   :

2. በዚህ መሰረት እያንዳንዷ አባል በስራ እና መኖሪያ ቦታዋ ፓርቲዉን እና ሴቶች ሊግን በእዉቀት፣ በገንዘብና በጉልበት መደገፍ የሚፈልጉ ፈቃደኛ ደጋፊዎች የማፍራትና የጋራ አደረጃጀት ፈጥሮ የመንቀሳቀስ ኃላፊነት አለባት፣
3. ከመኖሪያ ቤቱና መስሪያቤቱ ውጪ በደጋፊነት ለመደራጀት ፈቃደኛ የሆነች ሴት ካገኘች ደጋፊዋ በምትኖርበት ወይም በምትሰራበት አካባቢ ለሚገኝ ህዋስ ስሙ እንዲተላለፍና በአካባቢው እንዲደራጅ የማድረግ ኃላፊነት ይኖርባታል፣
4. እያንዳንዱ ደጋፊ ለመሆን ፍቃደኝነቷን ያረጋገጠች ግለሰብ ከሚቀራረቡትና ከሚስማሙት ሴቶች ጋር እንዲትደራጅ ይደረጋል፣
5. የደጋፊዎች ቡድን በተደራጁበት የደጋፊዉ ቡድን አባላት በተመረጠ፣ ተቀባይነትና የተግባር መሪነቷ የተረጋገጠች መሪ የሚመራ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 71. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ የደጋፊዎች ቡድን ተልዕኮ

1. የፓርቲው እና የሴቶች ሊግ ደጋፊዎች ቡድን አዳዲስና አስፈላጊ የሆኑ ሀሳቦችን የሚያገኙበት መድረክ ሆኖ ያገለግላል፣
2. የፓርቲው እና የሴቶቸ ሊግ ደጋፊዎች ለፓርቲው ሊያቀርቡ የሚፈልጓቸዉ ጉዳዮች፣ አስተያየቶች፣ መስተካከል ያለባቸዉ አመላከከቶችና አሰራሮች፣ የሚያቀርቡት ገንቢ ሐሳቦችና ነቀፌታዎች፣ ሲኖሩ የሚያመቻች መድረክ ሆኖ ያገለግላል፣
3. ፓርቲው እና ሴቶች ሊግ ከጠቅላላ ሴቶችና ምሁራን ጋር የሚኖረዉን ግንኙነት የሚያስተሳስር መድረክ ሆኖ ያገለግላል፣
4. በሂደትና በሙሉ ፈቃዳቸዉ ወደ ፓርቲው እና ቀጥሎም ወደ ሴቶች ሊግ የሚቀላቀሉ አዳዲስ ሴት አባላት የዕጩ አባላት መመልመያ መድረክ ሆኖም ያገለግላል፣
5. ለፓርቲው እና ሴቶች ሊግ የሚያስፈልገው የእዉቀት፣ ጉልበትና የገንዘብ ድጋፍ ተጨማሪ አቅም ሆኖ ያገለግላል፡፡

## አንቀጽ 72. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ የአባላትና ደጋፊዎች ቡድን አሰራር

1. የደጋፊዎች ቡድን ከተመሰረተ በኂላ የስብሰባና የውይይት ጊዜ፣ ከሴቶች ሊግ ያለው ግንኙነት፣ ሌሎችም የሚመለከት አሰራር ራሱ ይወስናል፣
2. የአባላትና ደጋፊዎች ቡድን በፍላጎትና መግባባት የሚመሰርት ይሆናል፣
3. የደጋፊዎች ቡድን አባላት የፓርቲው አባልሆነው በቀጣይም ወደ ሊጉ አባል መሆን በሚፈልጉበት ጊዜ ጥያቄያቸው በቀጥታ በአቅራቢያቸው ለሚገኝ ህዋስ ያቀርባሉ፡፡ ህዋሱ ያለውን ውሳኔ ይገልፅላቸዋል፣

4. በእያንዳንዱ ህዋስ ስር የተደራጁ የደጋፊ አባላት ዝርዝር ማህደራቸው በሊጉ መሰረታዊ ድርጅት የአደረጃጀት ኃላፊ ይቀመጣል፡፡ በየጊዜው ይታደሳል፣
5. የደጋፊዎች ቡድን አባላት አስተያየታቸው ለሚመለከተው አመራር ይሁን ለኮንፍራንስ መላክ ሲፈልጉ በአቅራቢያቸዉ ላለ የሊግ መዋቅር ወይንም እንደ አስፈላጊነቱ ይመለከተዋል ብለዉ ለሚያምኑት የፓርቲ መዋቅር ማቅረብ ይችላሉ፣
6. የደጋፊዎች ቡድን በተስማሙበት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ስለቡድናቸው የስራ አፈፃፀም ነፃ ሁነው ይወያያሉ፡፡ የዉይይታቸዉን ውጤት በአቅራቢያቸዉ ላለና ለሚደግፉቸዉ የሊግ መዋቅር እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 73 ፡ **የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ** አባላት በሴቶች ልማት ቡድን ውስጥ የሚኖራቸው ሚና፣

ይሴቶች የልማትና ለውጥ ስትራቴጅን እና ሌሎች የልማት እና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ስትራቴጅዎችን ወደ ተግባር በመቀየር ድህነትን የምንዋጋበት ዋነኛው መሣሪያ የሴቶች የልማት ቡድን መሆኑን ታሳቢ በማድረግ የሊግ  አባላት በዚህ ዙሪያ የሚጫወቱትን ሚና በግልጽ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው፤ በዚሁ መሠረት:-

1. ይበለጽግና - ርቲ የሴቶች ሊግ አባላት በአካባቢያቸው ባለው በአንድ የልማት ቡድን በመታቀፍ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡
2. የልማት ቡድኗ በምታደርገው ሁለገብ እንቅስቃሴ ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ይኖርበታል፤
3. በአንድ የልማት ቡድን ውስጥ ያሉ የሊግ አባላት ሴቶች የድርጅት አባል ያልሆኑ ሴት አርሶ አደሮችን ተከፋፍለው መልካም የሆኑ ልምዶችን በማስተላለፍ ሁሉም የቡድኑ አባላት የማስፋት ስትራተጅው ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፡፡
4. ከሌሎች የሴቶች ልማት ቡድኑ አባላት ጋር በመሆን በኅረበት አደረጃጀት ታቅፈው መንቀሳቀስና የግንባር ቀደምነት ሚናቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

## **አንቀጽ 74፡ ውህደቱን በሁሉም ሊጉ መዋቅሮች በአደረጃጀት ተግባራዊ ለማድረግ የሚኖሩ አደረጃጀቶች**

1. በየክልሉ ከውህደት በፊት የነበሩ አባል ሊጎች የነበሩ አዴፓ ሴቶች ሊግ ፣ ኦዴፓ ሴቶች ሊግ፣ ደኢህዴን ሴቶች ሊግ ድሬድዋ እና አዲስ አበባ ሴቶች ሊግ መዋቅሮች እንዲሁም አጋር ሊጎች የነበሩት የሶዴፓ፣ የአብዴፓ፣ የቤጉዴፓ፣ የጋህዴፓ እና የሀብሊ ሴቶች ሊጎች ውህደቱ ከተፈፀመ በኂላ ህጋዊ ህልውናቸው ስለተቋረጠ በየክልሉ የነበሩ አደረጃጀቶቻቸው በየሚገኙባቸው ክልሎች በየደረጃዉ ባሉ የብልፅግና ሴቶች ሊግ አደረጃጀቶች ታቅፈው ይንቀሳቀሰሉ

2. በተራ ቁጥር አንድ በተጠቀሰው መሰረት በክልል ደረጃ ያሉ አደረጃጀቶች በክልሉ የብልፅግና ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት ባለው አደረጃጀት ውስጥ የሚታቀፉ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ በዞን፣ በወረዳ፣ በከተማ፣ በቀበሌ፣ በመሰረታዊ ድርጅት እና በህዋስ ደረጃ ያሉ አደረጃቶችች በክልሉ ባሉ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ፣ የቀበሌ አባላት በሴቶች ሊግ የመሰረታዊ ድርጅቶች እና ህዋሳት ውስጥ ባሉ ሴቶች ሊግ ታቅፈው የሚደራጁና የሚንቀሳቀሱ ይሆናል፡፡

3. በተራ ቁጥር ሁለት የተጠቀሰውን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ቀደም ሲል የተደራጁት በመኖሪያ ቦታ የነበረ ከሆነ በሚኖሩበት አካባቢ ባሉ አደረጃጀቶች እንዲታቀፉ ይደረጋል፡፡ አደረጃቶቹ በሥራ ቦታ የተደራጁ ከነበሩ በሚሰሩበት ተቋም ባሉ አደረጃቶች ውስጥ ታቅፈው እንዲደራጁና እንዲንቀሳቀሱ ይደረጋል፡፡ ባሉበት መኖሪያ ቦታ ወይም የሥራ ቦታ የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አደረጃጀት ከሌለ በሚቀርባቸው ቦታ እና ተቋም ታቅፈው እንዲደራጁና እንዲንቀሳቀሱ ይደረጋል፡ ፡

4. ከተራ ቁጥር 1-3 የተዘረዘሩትን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት በተለይ ደግሞ በየአደረጃጀቶቹ የሚካሄደዉን ግንባታ ዉጤታማ ለማድረግ የቋንቋዎች አጠቃቀም ወሳኝ ነዉ፡፡ በመሆኑም በህዋሳትና መሰረታዊ ድርጅቶች በሚካሄዱ ዉይይቶች እና በተለያዩ ደረጃዎች በሚዘጋጁ ስልጠናዎች የሰነድ ዝግጅትና ዉይይቶቹ የሚመሩበት አግባብ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ እና ሴቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ የተቀመጠዉን ተግባራዊ በሚያደርግና የቋንቋዎችን ብዝሀነት በአግባቡ ግምት ዉስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባዋል፡፡

5. የፌዴራል ተቋማት፤ በሕዋስና በመ/ድርጀት የሚደራጁ ይሆናል፡፡ አደረጃጀቱም በሶስት ክላስተር ማለትም በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና አስተዳደራዊ ዘርፎች ይደራጃል፡፡ ክላሰተሩን የሚመሩ 5 አባላት ያሉት ኮሚቴ በአስተባባሪ ኮሚቴው ይመደባል፡፡ የሚደራጁ ተቋማት ተጠሪነታቸው ለሊጉ ዋና ጽ/ቤት ነው፡፡ የፌዴራል ተቋማት የሊጉ አሰተባባሪ ኮሚቴ 9 አባላት ያሉት ሆኖ በሊጉ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አሰፈጻሚ ደረጃ ያሉ አመራሮች በፌደራሉ የሊጉ አስተባባሪ ኮሚቴ ይመደባሉ፡፡ ኮሚቴው ሰብሳቢ፣ ፖለቲካ ዘርፍ፣ አደረጃጀት ዘርፍ፣ ፋይናንስ ዘርፍ የሚሉ የስራ ክፍፍሎች ይኖሩታል፡፡

6. በክልል ደረጃ የክልል ሴክተር በሶስት ክላስተር ማለትም በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና አስተዳደራዊ ዘርፍ ይደራጃል፡፡ ክላሰተሩን የሚመሩ 5 አባላት ያሉት ኮሚቴ ይኖራል፡፡ በሁሉም የክልል ሴክተር ሊጉን በሚመለከት የፖለቲካ አመራር የሚሰጡ የክልል ሴክተር የሊጉ አመራር ኮሚቴ 7 አባላት በሊጉ አስተባባሪ አመራር ይመደባል፡፡ ተጠሪነቱ ለክልሉ ሊግ ጽ/ቤት እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በየክላስተሩ በቋሚነት ሁለት ሁለት አመራሮችን በመመደብ የዕለት ተዕለት የክትትልና ድጋፍ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

7. አዲስ አበባና ድሬዳዋ የከተማ /አስተዳደሩ ሴክተር በሶስት ክላሰተር ማለትም በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና አስተዳደራዊ ዘርፍ በሚል ይደራጃል፡፡ ክላሰተሩን የሚመሩ 5 አባላት ያሉት ኮሚቴ

ይኖራል፡፡ ሁሉንም ሴክተር ሊጉን በሚመለከት የሚመሩ ደግሞ 7 አባላት ኮሚቴ በሊጉ አሰተባባሪ ይመደባል ተጠሪነቱ ለከተማው/ለአስተዳሩ ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡ በየክላስተሩ የዕለት ተዕለት የክትትልና ድጋፍ ስራ የሚያከናውኑ ሁለት ሁለት የሊግ አመራሮችን በቋሚነት በመመደብ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

8. ከአዲስ አበባ ውጭ ክፍለ ከተማ ያላቸው ከተሞች ለዞን/ለወረዳ/ለልዩ ወረዳ ተጠሪ የሆኑ ከተሞች በሚል የተቀመጠው እንደደረጃቸው የሚያገለግል ሲሆን ድሬዳዋ የገጠር ክላስተር ወረዳ የሚለው ይጠቀማል፡፡

ግንቦት 2012 ዓ.ም